ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

የ2006 ዓ.ም. የዩኒቨርሲቲው ዕቅድ ባለፉት ዓመታት የተገኙ ልምዶችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ለአተገባበርና ክትትል አመችነት ሲባል በዝግጅት፡ ትግበራ እና ማጠቃለያ ምዕራፎች የተከፋፈለ መሆኑ ይታወሳል፡፡

በመጀመሪያዉ ሩብ ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስለነበረ በወቅቱ የተቀዱትንና የተከናዋኑትን በየድርሻቸዉ በዝርዝር ቀርቦ ዉይይት ተደረጎበት የታዩ ክፍተቶች ላይ በቀጣዩ ሩብ ዓመት ወይም በትግበራዉ ምዕራፍ ትኩረት ሰጥቶ ለመተግበር ታቅዶ ወደ ስራ የተገባበት ሁኔታ ነበረ፡፡ በዚሁ መሠረት የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፀፃም በዚህ ሪፖርት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

የሪፖርቱ ዓለማ

የዚህ ሪፖርት ዓለማ ዩኒቨርሲቲዉ በ6 ወር ወይም በግማሽ ዓመት ዉስጥ ያከናወነቸዉን ሥራዎችን የሚገመግምበትና ያለበትን ደረጃ የሚያዉቅበት ነዉ፡፡

- የዩኒቨርሲቲዉ ዕቅድ አፈፃፀም ለመዳሰስና እንዲሁም ጠንካራና ደከማ ጎኖቹን ነቅሶ ለማዉጣት፡፡
- ኮሌጆች ወይም የሥራ ክፍሎች የሚማማሩበትና በዩኒቨርሲቲዉ አላማ ማስፈፀም ላይ የጋራ አቃም የሚይዙበት ነዉ፡፡
- በመጨረሻም አግባብ ያለዉ አስተየየት ለመስጠትና የመፍትህ አማራጮችን ለማስቀመጥ ነዉ፡፡

የሪፖርቱ አቀራረብ

ይህ ሪፖርት ሁለት አይነት የረፖርት አቀረረብ ዘዴ የተከተለ ሲሆን እነሱም በአሃዝና በአገላለፅ ናቸዉ፡፡ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የተጠቀምነዉ ዘዴ ቅድሚያ መጠይቆችን በማዘገጀትና በተዘገጀዉ መጠይቆች ላይም ኮሌጆችና ሌሎች የሥራ ክፍሎች እንዲሞሉ በማድረግ ነበረ፡፡ መረጃዉ የተጠናከረና እዉነተኛ እንዲሆን ሪፖርት አቀነባሪ አካላት በአካል በቦታዉ በማድረስ ለሀለፊዎችና ቁልፍ ለሆኑ ሠራተኞች የቃል ጥያቄ በመጠየቅ መረጃዎች ተሰባስበዋል፡፡ ይህንን መረጃ በፎቶ የተደገፈ ለማድረግ ፎቶ በማንሳት የተቀነባበረ ሪፖርት ነዉ፡፡ ይህ ሪፖርት ለአንባቢዉ አስረጅ እንዲሆን በግልፅ ቋንቋ የተቀነባበረና በተቻለ መጠን ሪፖርት የሚቀርብበትን ዘዴ የተከተለ እንዲሆን ዝርዝር የሪፖርቱ ክፍሎች በሰንጠረዥ፤ በግራፍ እና በግልፅ በፅሁፍ የቀረበ ሪፖርት ነዉ፡፡

ይህ የግማሽ አመት ሪፖርት በመጀመረያዉ ሩብ አመት አፈፃፀም ግምገማ ላይ የዩኒቨርሲቲዉ ቦርድ የሰጠዉ አስተያየትና ያስቀመጠዉ አቅጣጫ እንደግብኣት ተወስዶ በሪፖርቱ ዉስጥ ተካቶ ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሪፖርቱ ላይ የሰጡት ግብረ-መልስ እንደበጎ መልስ ተወስዶ እንደግብኣት በመጠቀም በሪፖርቱ ዉስጥ እንዲከተት ተደርገዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲዉ ቦርድ ያስቀመጠዉ አቅጣጫ

ዩኒቨርሲቲዉ የመጀመረያዉ ሩብ አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በዩኒቨርሲቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ለዩኒቨርሲቲዉ ቦርድ አቅርቦ ቦርዱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ካደመጠ ቦኃላ መሰረታዊ አስተያየት በመስጠት የራሱን አቅጣጫ አስቀምጥዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲዉ ቦርድ ያስቀመጠዉ አቅጣጫም እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡

የዩኒቨርሲቲዉ ያስቀመጠዉን ዓለማ ከግብ ለማድረስ ያሳየዉ ጠንካራ አቋምና የተገበራቸዉ አኩሪ ታግባራት የሚመሰገንበት ሥራ በመሆኑ በዚሁ መልኩ መቀጠል እንደለበት በጎ ሀሰብ በመስጠት ነገር ግን አሁንም ቢሆን የተፈለገዉ ደረጃ ለማድረስና እይተዉን ዕዉን ለማድረግ በቦርዱ አይን የተቀኙትን በዩኒቨርሲቲዉ ጠንካራ ትኩረት ያልተሰጠበቸዉ ግን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ስራዉ ቢሰራም በሪፖርቱ ዉስጥ ስላልተካተቱ በቀጣዩ ሩብ አመት ተስተካክሎና ተጠናክሮ በሪፖርቱ ዉስጥም ተካቶ እንድቀርብ በማለት የትኩረት ቁልፍ ቦታዎች ናቸዉ ያለቸዉን ነጥቦች ለይቶ አስቀምጠዋል፡፡

እነርሱም፡-

1. በመልካም አስተዳደር ላይ የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም በሪፖርቱ ዉስጥ ብዙም ስላማይታይ በቀጣዩ ሩብ አመት ዝርዝር ታግባራት በግልፅ ተለይቶ በሪፖርቱ ዉስጥ ተካቶ እንዲቀርብ፤
2. ሰላማዊ የመማር መስተማር ሂደት ኢንዲኖር ለማድረግ በድህንነት ላይ የተሰሩ በጎ ጅምሮች ቢኖሩም በተጠበቀዉ መልኩ ስለአልተፈፀመ ተጠናክሮ ኢንድቀጥልና በሪፖርት ዉስጥም ተካቶ እንዲቀርብ፤
3. በብሔር ፤ በሃይማኖት ልዩነት ላይ ያለዉ ልዩነትን ለማጥባብ የተወሰደ እርምጃ ቢኖርም በሪፖርቱ ዉስጥ በሰፊዉ ተካቶ አለመቅረቡ፤
4. በልማት ሠራዊት ግንባታ ላይ ስራ እየተሰራ ነዉ ከማለት በሻገር ተሰርቶ የሚታይ ነገር በሪፖርቱ ዉስጥ አይተይም
5. ከጂማ ከተማ መስተዳድርና ማህብረሰብ ጋር ዩኒቨርሲቲዉ ያለዉ ግንኙነት በበጎ ጎኑ የሚወሰድ ጉዳይ ሆነዉ እያለ እንደ ዩኒቨርሲቲ ባለዉ ዕምቅ የተማረ የሰዉ ሀይል ተጠቅሞ በከተማዉ ላይ ያሳየዉ ለዉጥ ብዙም ስለማይታይ ለወደፍቱ ከከተማዉ መስተዳድር ጋር በመሆን በከተማዉ ለዉጥ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችል ስራ ተሰርቶ መተያት አለበት የሚሉ ናቸዉ፡፡

   እነዚህን በጎ አስተያየቶች እንደ ገንቢ ሃሳብ በመዉሰድ ዩኒቨርሲቲዉ በዚህ ሩብ አመት ዉስጥ ለተፈፃምነቱ በመንቀሰቀስ የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎችን በዚህ ሪፖርት አካቶ አቅረቧል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2. የጂማ ዩኒቨርሲቲ ራዕይ፡ ተልዕኮና የትኩረት አቅጣጫዎች

ራዕይ

የጂማ ዩኒቨርሲቲ ራዕይ በሚሰጠዉ ትምህርትና ሥልጠና፤ በሚያካሂደዉ ምርምርና ስኮላርሽፕ እንዲሁም ለሕበረተሰቡ በሚሰጠዉ ሙያዊና የምክር አግልግሎት የላቀ ጥራትና ብቃት ኖሮት በአገሪቱ መሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፤ በአፍሪካ የታወቀና በአለምም የተከበረ የትምህርት፡ የምርምርና አገልግሎት ማዕከል በመሆን በአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ልማት ዉስጥ ጉልህ አስተዋፅዖ የሚያበረክት የልማት አጋር ሆኖ ማየት ነዉ፡፡

ተልዕኮ

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ ጥራትና አግባብነት ያለዉ ትምህርትና ሥልጠና በቅድመ ምረቃ፡ ድህረ ምረቃና ሙያ ማሻሻያ ደረጃዎች፤ በመደበኛ፡ በተከታታይና ርቀት መርሃ ግብሮች በመስጠት አገሪቱ ለልማትና ዕድገት የምትፈልገዉን የሰለጠነ ሰዉ ኃይል በብዛትና ጥራት ማፍራት፤ የአገሪቱን ዋነኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት፡ ዕዉቀትን በማመንጨት፡ በማሳደግና በመጠበቅ ላይ ያተኮሩ ምርምሮችን ማካሄድ፤ እንዲሁም ቀልጣፋና ተገልጋዩን የሚያረኩ ሙያዊና የምክር አገልግሎቶችን በመስጠት በህብረተሰቡ ሁለንተናዊ ልማትና ድህነትን በመቅረፍ እንቅስቃሴ ዉስጥ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ነዉ፡፡

ዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎቹን የትምህርትና ሥልጠና ፍልስፍናዉ በሆነዉ የህብረተሰብ አቀፍ ሥልጠና ትምህርት አሰለጣጠን ዘይቤ ዉስጥ እንዲያልፉ በማድረግ የትምህርት አሰጣጡ ተማሪ ተኮር፡ ከተግባር የተገናዘበና ችግር-ፈች እንዲሁም ህብረተሰቡን የሚያሳትፍና የሚደግፍ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፡፡

መሠረታዊ ዕሴቶች

- ጥራትና አግባብነት ያለዉ ትምህርት፡ ምርምርና አገልግሎት (Quality and Relevance)
- የላቀ ብቃት (Excellence)
- ሕብረባህላዊነት፡ መቻቻልና መቀራረብ (Diversity, Tolerance and Inclusiveness)
- ለስራዓተ-ፆታ ትኩረት መስጠት (Gender Sensitivity)
- ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማስፋት (Equity and Access)
- የመደጋገፍና የቡድን ስሜት (Collegiality and Team Spirit)
- ግልጽነትና ተጠያቂነት (Transparency and Accountability)
- ታማኝነትና ሃቀኝነት (Honesty and Integrity)
- ማህበረሰቡን ማሳተፍና ማስቻል (Community Involvement and Empowerment)
- በትብብርና አጋርነት መስራት (Networking, Collaboration and Partnership)
- ወጪ ቆጣቢነትና ዉጤታማነት ዋና ዋናዎቹ ዩኒቨርሲቲዉ የሚገዛባቸዉ መርሆቹ ናቸዉ፡፡

- በተልዕኮ ስኬት ላይ የተመሰረተ ታዋቂነት
- አሳታፊ አስተዳደርና የሕግ የባላይነት
- ዴሞክራሲና የባህል ብዙህነት
- ለምስጉን ሰዉ ዕዉቅና መስጠት
- እዉነትን የማሻትና እዉነትን የመግለጽ ነፃነት
-

የትኩረት አቅጣጫዎች (Strategic Themes)

ጂማ ተልዕኮዉን ለማሳካት ከራዕዩም ለመድረስ ኢጋሾ የሆኑ የትኩረት አቅጣጫዎችን በዉጤት ተኮር ስትራጂያዉ ሰነዱ አስቀምጧል፡፡ እነዚህም የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

- የላቀ አካዳሚክስ (Academic excellence)
- የላቀ ምርምርና የእዉቀት ሽግግር (Excellence in research and technology transfer)
- የላቀ አገልግሎት (Excellence in service)
- መልካም አስተዳደር (Good governance)

ምዕራፍ ሦስት

3. የ 2006 ዓ.ም. መንፈቀ -አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ክፍል አንድ

3.1. የፕሮግራም በጀቲንግ እና ሚዛናዊ ዉጤት ተኮርን (BSC) ያገናዘበ የ6ወር የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

የዚህ አመት ዕቅድ የተዘጋጀዉ በዉጤት ተኮር ስርዓት መሰረት የተሰናዳዉ የዩኒቨርሲቲዉ ስትራቴጃዉ ሰነድ እንዲሁም የፕሮግራም በጀቲንግን መነሻ በማድረግ እንደሆነ ይታወሳል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዉ በስተራቲጅክ ዕቅድ ዘመኑ ያስቀመጣቸዉን አራት የትኩረት አቅጣጫዎች (የልህቀት ምሶሶዎች) መሰረት በማድረግ በተዘጋጁ አራት ዋናዋና ፕሮግራሞች የአመቱ ዕቅድ ተቀምጦ የነበረ ሲሆን፣ የዚህ መንፈቀ አመት አፈፃፀም ሪፖርትም በነዚህ አራት ፕሮግራሞች (አበይት ተግባራት) ስር ለዚህ ግማሽ ዓመት የታቀዱ ስራዎችንና የነሱን ክንዉን የሚገልጽ ይሆናል፡፡

3.1.1. ፕሮግራም አንድ/ የትኩረት መስክ፡- መማር መስተማር

<u>ስትራቴጅክ ዓላማ፡-</u> ጥራቱንና አግባብነቱን የጠበቀ፡ ተደራሽነቱ የሰፋና ፍትሃዊ ትምህርት በመስጠት የደንበኞችን/ባለድርሻ አካላትን እርካታ፡ አምነትና ጥቅም ማሳደግ

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት፣-ትምህርታቸዉን የተከታተሉ ተማሪዎች ብዛት 46000 ሲሆን ከዚህ ዉስጥ የሚመረቁት 8000 ይሆናል፡፡

የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት

- የአካዳሚክ ካላንደር ፀድቆ ለሁሉም ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎች እንዲሁም መምህራን እንዲደርስ ተደርጃል
- የትምህርት ክፍለ ጊዜ ዝግጅትና የኮርስ ድልድል ተጠናቆ የመማር ማስተማር ሂደቱ እየተካሂደ ነው፡፡
- ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ግዢ ለመፈፀም ሂደቶች በከፊል ተከናውኗል
- ነባር ተማሪዎችን በመቀበል first day first class መርህን ተከናውኗል
- በአመቱ መጨረሻ በተበለዉ ውጤት ላይ ለማድረስ በዚህ ግማሽ አመት 7980 አድስ ገብ ተማሪዎችን በተለያዬ የትምህርት መስክና ሙያ ተቀብሎ እያስተማረ ይገኛል፡፡ 1809 ተማሪዎችን ደግሞ በተለያዬ ሙያ በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ በማስመረቅ ወደ ህብረተሰቡ ገብተዉ ለህብረተሰቡ አገልግሎት

ኢንዲስጡ ሲያደርግ ዩኒቨርሲቲዉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽንን ዓለማ በትምህርት ሴክተር በኩል ለማሰከት ያደረገዉ አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

- የጂማ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት በ GTP's Priority Sectors ተብለው በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለዩ የስልጠና መርሀ-ግብሮች የትምህርት ስርዓት (curricula) ቀርፆ በኢንዱስትሪው የሚገኘውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር ለመቅረፍ ወደስራ መግባቱ ግልፅ ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በ Infrastructure Development Sectors:- በ መንገድ ፣ በፖወር እና ኢነርጂ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን ፣በውሃ አቅርቦት እና ኢሪጌሽን ዙሪያ ከሚመለከታቸው ሴክተሮች እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የመማር ማስተማር ፕሮጀክት ተቀርፆ በአሁኑ ሰዓት ከ300 በላይ የሚሆኑ ነበርና አድስ ተማሪዎችን በቁጥር ሰባት በሆኑ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ተቀብለዉ እያሰለጠን ሲሆን በያዝነው ዓመትም ወደ 90 የሚጠጉ የድህረ ምረቃ ባለሙያዎች በ Priority Sectors ለምረቃ ዝግጁ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡
- ሌላው የ GTP's Priority የ Environmental and Climate Change Sectors ሲሆን በዚህ ዙሪያም የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የጀመርን ሲሆን መምህራኑም ሰፊ የምርምር ስራዎችን በማከናወን በአሁኑ ሰዓት አራት የPhD ምሩቃን በዚህ ዘርፍ ትምህርትታቸውን አጠናቀው ወደ ስራ እየገቡ ይገኛል፡፡
- በ Industries Sectors (Sugar Industries, እና Chemical Industries) ለማስመረቅ ደርሷል ወደ 400 የሚጠጉ የቅድመ መረቃ ዲግሪ መደበኛ ተማሪዎችን ለምረቃ ብቁ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ ከዚህ በተጨማረ የዩኒቨርሲቲ-ኢንደስተር ትስስሩን በከፍተኛ ሁኔታ ለማጠናከርም በየአመቱ በኢንጂነሪንግ ትምህርታቸው የሚከታተሉ ተማሪዎችን በሀገሪቱ በሚገኙ ተጓዳኝ ኢንዱስትሪዎች እና ካምፓኒዎች ጋር በመሆን ለአንድ ሙሉ ሴሚስተር (16 ሳምንት) በጋራ የተግባር ልምምድ (Internship) እንዲያከናውኑ በማድረግ ላይ ስንሆን በአሁኑ ሰዓትም በቁጥር 55 ከሚጠጉ ተጓዳኝ ኢንዱስትሪዎች ጋር ከ 1500 በላይ ተማሪዎችን እና መምህራንን ከኢንዱስትሪው ሠራተኞች ጋር በማስተሳሰር እየሰራን እንገኛለን፡፡ ከአብዛኛው ኢንዱስትሪዎች የምናገኘው ግብረ መልስም እጅግ የሚያበረታታ ሲሆን ካለን የተማሪ ብዛት የተነሳ በቂ ኢንዱስተሪዎችን (ካምፓኒዎችን) አግኝቶ ተማሪዎቻችንን ለመላክ ተደጋጋሚ ችግር ገጥሞናል፡፡
- አድስ ገቢ ተማሪዎች ለአከባቢዉ አድስ ስለመሆናቸዉ ዩኒቨርሲቲዉ ግንዛቤ ዉስጥ በማስገበት ከዚህ በፊት ሲደረግ በነበረዉ መሠረት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት በደህነተችዉ ላይ ምንም አይነት ችግር ሳይደርስ ወደ ዩኒቨርሲቲዉ ኮሚንቲ ኢንዲቀላቀሉ አድረገዋል፡፡

- የዩኒቨርሲቲዉ የተማሪዎች ህብረትና ሌሎች ክበባት ለአድስ ገቢ ተማሪዎች ለደህነታቸዉ ተብሎ ጠንካራ አቀባበል አድርጎላቸዋል፡፡

- የከተማዉ ማስተዳደርም ተማሪዎቹ ያለምንም የደህንት ችግር ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ከፍተኛ የሆነ ትብብር አድርገዋል፡፡

- ለአድስ ገቢ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲዉን ህጎች፤ ደንቦች፤ ሥርዓቶችና ተማሳሰይ ጉዳዮች ላይ የግንዘቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርተዋል፡፡

- ተማሪዎቹ የሚፈልጉትን የትምህርት መስክ በፍላጎት ኢንዲመርጡ ለማድረግ የሁሉም ኮሌጆች ዲንን ጨምር የትምህርት ክፍል ኃላፍዎች የየትምህርት ክፍለቸዉን መረጃ ለተማሪዎቹ ገለፃ አድርገዋል፡፡

- በዚሁ መሠረት ተማሪዎቹ የትምህርት መስክቸዉን መርጠዉ መደበኛው የመማር መስተማር ሥራ ተጀምሮ በተጠናከረ መልኩ እየተሰጠ ይጋኛል፡፡

- ተመራቂ ተማሪዎች በተቀመጠለት ዕቅድ መሠረት በተየዘዉ ቀነቀጠሮ ምርቃቱ ኢንዲከናወን የተማሪዎችን ግሬድ በማሰባሰብ የሚመረቁትና የማይመረቁትን በመለየት በሴኔት በማስፃደቅ ለምርቃቱ ኢንዲበቁ ተደርጎ ምርቃቱ ተከሄድዋል፡፡

- በሁሉም ኮሌጆች የተከታታይ የተማሪዎች ምዘና ሥርዓት ተዘርግቶ መምህራኑ በፅንሰ ሐሰቡ ላይ በመስማማት ምዘናዉ እየተከሄደ ይጋኛል፡፡ መልካም ለዉጥም በተማሪዎች ላይ አሳይተዋል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች አብዘኛዉን ግዜያቸዉን በጥናት ላይ ስለምያሳልፉ አንደኛ ተማሪዎቹ በግዜ ብዛት ምክንያት ወደ መጥፎ ነገር እንደያስቡ ተቆጥበዋል ሁለተኛ አብዛኛዉን ግዜያቸዉን በዉዴታም ይሁን በግዴታ በጥናት ላይ ስለምያሳልፉ ደካማ የተበሉ ተማሪዎች ራሳቸዉ ጥሩ ዉጤት እያስመዘገቡ ይጋኛሉ፡፡

- በሁሉም ኮሌጆች የመጀመሪያ ሲሚስቴር ሊጠናቀቅ ስለሆነ የፈተና ፕሮግራሞች የማዘገጀትና ፈተናዎች ኢንድዘጋጁ ተደርጎ ሁሉም ተጠናቀዋል፡፡

- በግማሽ ዓመቱ የታቀደዉ የትምህርትና የፈተና ፕሮግራሞች አወጣጥ፤ የፈተና ዝግጅትና የዉጤት ግምገማና አፈፃፀም በዕቅዱ መሠረት መቶ በመቶ ተከናዉነዋል፡፡

- የነለ5 አደረጃጀት ተጠናቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

የመማር መስተማር ሂደቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን የኢይሲቲ አገልግሎትን ማጠናከር ወሳኝና አማረጭ የሌለዉ መንገድ ነዉ፡፡ በዚሁ መሠረት በዚህ ግማሽ አመት የሚከተሉት ሥራዎች ተከናዉነዋል፡፡

- በርካታ የተማሪ ቁጥር ያለዉ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ካምፓስ በኔትዎርክ አገልግሎት ለማጠናከር ዕቅድ ተይዞ 40 ኮምፒዉተር በሚይዝ አንድ ክፍል ዉስጥ ሙሉ የኔትዎርክ ዝረጋታ ሲደረግ በተጨማሪም በመማሪያ ክፍሎች አከባቢ ገመድ አልባ የኔትዎርክ ኢንተረኔት አገልግሎት ጀምሯል፡፡
- አዳድስ ስማርት ክላሶችን ለማቋቃምና እንድሁም ነባሮቹን ለማጠናከር በተያዘዉ ዕቅድ መሰረት 46 የመማሪያ ክፍሎች ወደ ስማርት ክላስ እንዲቀየሩ ተደርጓል፡፡

- **ለተማራ- ችና መምህራን የተጀመረው የፋይል ስቶሬጅ ስራ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ስንትራል ፋይል ስቶሬጅ ሲስተም በማዕከል ደረጃ ተቋቁሟል፡፡**
- **በቴክኖሎጂ ኢንሲቲትዩትና በዋናዉ ግብ ስምንት የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ ሲስተም የማትከል ስራ ለማስ□□ም** የተለያዩ ግብዓቶች ግዥ **ተከናዉኗል**፡፡
- ለአምስት ዩኒቨረስቲዎች ረጅስትራርን በተመለከተ የልምድ ልዉዉጥ ማካፈል ስራ ተካሂዷል

- የረጅስትራር ሲስተም ሶፍት ዌር አመሰራረት ተጠናቆ አገልግሎት ላይ መዋል ጀምሯል
- የመማሪያ ክፍሎች ድልድል በሶፍት ዌር በመታገዝ ተካሂዷል
- ዩኒቨርሲቲዉ ለወደፊቱ የተማሪዎችን የዉጤት ምዘና ስርዓትን በቴክኖሎጅ የተደገፈ እንዲሆን ለማድረግ የኦንላይን ተከታታይ ምዘና ስራ ላይ ለማዋል በታቀደዉ መሠረት የነኛ ዓመት ተማሪዎች ዉጤት አንላይን ኢንዲለክ ተደርግዋል ለስኬተማናቱም በሶፍትዌሩ ላይ ለ225 መምህራን ስልጠና ወስደዋል፡፡
- የዩኒቨርሲቲዉ መደበኛ ተማሪዎች የተቋሙን ኢሜይል አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ በታቀደዉ መሠረት ለ22000 መደበኛ ተማሪዎች ለእያንደንዳቸዉ የኢሜይል አካዉንት ተከፍቶለቸዋል፡፡ በቀጣዩ ሩብ ዓመት አካዉንታቸዉን አክትቭ በማድረግ ተማሪዎቹ የአገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ለመማር መስተማር ዋንኛና ግንባር ቀደም ተጠቀሽ የሆነዉ ሌለኛዉ የአገልግሎት ማዕከል ደግሞ ቤተመጽሐፍትን ማጠናከር ነዉ፡፡ በዚሁ መሠረት ዩኒቨርሲቲዉ በአመቱ ከአቀዳቸዉ ሥራዎች ዉስጥ የሚከተሉት ታግባራት በዚህ ግማሽ ዓመት ተከናዉነዋል፡፡

- የዩኒቨርሲቲዉ አብያተመጽሓፍት በ2005 ዓ.ም. ግዥ የተከሄደበቸዉና ነገር ግን ወደ ዩኒቨርሲቲዉ ያልገቡ በአርዕስት 4000 መጽሓፍትን ወደ ዩኒቫርሲቲ በማስገባት ለአገልግሎት ለማዋል ታቅዶ በዚሁ መሠረት በዚህ ግማሽ ዓመት 2467 መጽሓፍት ወደ ዩኒቨርሲቲዉ ገብተዉ የቴክንካል ሥራዎች ተሰርቶ ወደ ቅርንጫፍ ቤተመጽሓፍቶች ለአገልግሎት ሲላኩ ኮሌጆችም መጽሃፍቶቹ ስለማግበቱ ለማሰወቅ ሙሉ የመጽሐፍቶቹ ስም ዝርዝር ተልኮላቸዋል፡፡
- የቤተመጽሐፍት አገልግሎትን የለቀ ደረጃ ላይ ለማድረስ በተደረገዉ እንቅስቀሴ አንድ ስለአገልግሎት የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቅሞ በየግዜዉ በሁሉም ቤተመጽሐፍቶች ያለዉን የአገልግሎት ሂደትን በመከታተል እጥረት ወይም ችግር አለባቸዉ የተበሉትን ቦታዎች ለይተዉ በማዉጣት ለመፍተህ ያቀርባሉ፡፡ በዛዉ መሠረት የአብያተመጽሐፍቱ የበላይ አመራሮች በጉደዩ ላይ ጥናት በማድረግ አግባብ ያለዉ መፍትህ በአጭር ግዜ ዉስጥ ይሰጣሉ፡፡
- የቤተመጽሐፍት አገልግሎት ዲጅታላይዚድ ለማድረግና ተጠቃሚዎች አንላይን አገልግሎት ለመስጠት 5846 መጽሐፍቶችን ወደ ሶፍት ኮፒ በመቀየረ ወደ ኮሚፒዉተር ሲስተም እንዲቀየር በዓመቱ ታቅዶ በግማሽ ዓመቱ 1627 መጽሐፍቶች ወደ ሶፍት ኮፒ ተቀይረዋል፡፡ ይህ ቁጥር ከአመቱ ዕቅድ ጋር ስነፃፀር 27.83 በመቶ መከናወኑን ያሳያል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዉ ለወዳፍቱ የዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ የቤተመጽሓፍትን አገልግሎት በአካል ሄዶ ከማግኘት ጎን ለጎን የአንላይን አገልግሎትም ማግኘት እንድችሉ ለማድረግ ቤተመጽሓፍቱ ወደዚህ መስመር እየገባ ስለሆነ ማህብረሰቡን ማስልጠን መሰረታዊ ጉደይ ስለምሆን አብያተመጽሐፍቱ ለማህብረሰቡ ስልጠና ለመስጠት በቀደዉ መሠረት 400 ተማሪዎች በኢ-ላይብረሪ ዘሪያ ስልጠና ሲወስዱ 200 መምህራን ደግሞ ስለድጂታል ላይብረሪ ስልጠና ወስደዋል፡፡

- በግማሽ አመቱ 2500 የሚሆኑ የጥናትና ምርምር ዉጤቶች ወደ ሶፍት ኮፒ ተቀይሮ አገልግሎት በማስጠት ላይ ይጋኛል፡፡
- የዩቨርሲቲዉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና ሌሎች ማህብረሰብ ዉጣ ዉረድ የሌለበት ለአካል ጉዳተኞች የሚመች የቤተመጽሐፍት አገልግሎት እንደያገኙ ለማድረግ በታቀደዉ መሠረት ተከናዉኖ የአገልግሎት አሰጠጡም እየተጠናከረ ይጋኛል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዉ የራሱን ፍልስፍና ወደ ህብረተሰቡ በማዉረድ we are in the community የሚለዉን ሎጎ በተጨባጭ ዕዉን ለማድረግ በህብረተሰብ አቀፍ ትምህርት ፕሮግርም፡- በኢንተርንሽፕ፤ በፕራክቲከምና ፕሮፌሽናል ፕራክቲስ በዓመቱ 1700 ተማሪዎች እንድሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ በመጀመረያዉ ሩብ ዓመት 1400 ተማሪዎች ሲሰማሩ በዚህኛዉ ሩብ ዓመት ደግ 256 ተማሪዎች ተሰማርተዉ የትምህርቱን መሠረታዊ አለማ በህብረተሰቡ መከካል እንዲገባ ተደርግዋል፡፡
- የተጠናከረ የመማር መስተማር ሂደት ኢንዲኖር ለማድረግ በትምህርታቸዉ ጠንካራ፤ መካከለኛና ደከም የሚሉትን ተማሪዎች በዉጤተቸዉ መሰረት ታለይተዉ ከተወቁ ቦኃላ ጥሩ የአፈፃፀም ስብጥር በመካካላቸዉ እንድኖር ሦስቱም ከተነሪዎች የሚገኙበት ቡድን እንዲፈጠርና እንድደጋገፉ ነለ5 በማደረጃት 3300 ቡድን በዩኒቨርሲቲዉ ደረጃ ተቋቅመዋል፡፡
- ተማሪዎቹን የማደረጀት ሥራ ከተሰራ ቦኃላ ሁሉም ቡድኖች የየራሳቸዉ ቡድን መሪ እንዲኖራቸዉ ሲደረግ በየግዜዉ ግን ቡድን መሪዉ ይቀየራል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሁሉም ተማሪዎች የመሪነትን ክህሎት በዚሁ ደረጃ እንድጨብጡና ደፋር እንድሆኑ ለማድረግ ያህል ነዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ በቡድኑ ዉስጥ ጎልቶ እንዲታይና አቅማቸዉንም እንዲያጎለብቱ ለማድረግ የቡድን መሪ በመሆን እንድሰሩ ተደርግዋል፡፡ ለየቡዱኖቹም መምህር ተመድቦላቸዉ ችግር ባለበት ቦታ ላይ መምህሩ እንዲረዳቸዉ ተደርጓል፡፡
- በዚሁ መልኩ መምህራንም በምያስተምሩት የትምህርት ዘርፍ በኬዝ ቲም እንድደራጁ ተደርጎ በሁሉም ኮሌጆች ተደራጅቷል፡፡ በተጨማሪም በየትምህርት ክፍላቸዉም በልማት ቡድን እንዲደረጁ ተደርጎ 178 ቡድኖች ተደራጅቷል፡፡
- ሁሉም የዩኒቨርስቲው ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ ፤የየኮሌጅ ዲኖች፤የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ፤የተማሪዎች ተወካይ ፤ ዳይሬክተሮች ፤ቡድን መሪዎች በተገኙበት በትምህርት ልማት ሠራዊትና በነለ5 አደረጃጀት ፅንስ ሃሳብ ላይ በሁለት ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከነለ5 አደረጃጀት በኃላም የየቡዱኖች ዕቅድና አፈፃፀም ላይ የዩኒቨርሲቲዉ የበላይ አመራሮች በተገኙበት የየሁሉም ኮሌጆችና ሌሎች የሥራ ክፍሎች ሪፖርት ተሰምተዋል፡፡
- በነለ5 ለተደራጁ ተማሪዎች በቅርቡ የሚከታተል አማካሪ መምህር ተመድቦላቸዉ ባለባችዉ ችግሮች ላይ የቅርብ ምክር እንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡

- በያንዳንዱ የተማሪዎች ቡድንም ሆነ የመምህራን ቡድን ውስጥ ሱፐርቫይዘርና ፀሐፊ በመምረጥ በሳምንት አንድ ጊዜ ወይም እንደሁኔታው ያሉበትን ደረጃ ይገመግማሉ፡፡
- በዩኒቨርስቲ ደረጃም በኘሬዚደንቱ የሚመራ 7 አባላት ያለው የሱፐርቪዥን ኮሚቴ ተቋቁሟል
- ለሴት ተማሪዎች የማንበቢያና የኢንተርኔት አገልግሎት ፤የፎቶ ኮፒ አገልግሎት፤የመዝናኛ ክበብ አገልግሎት በየመኝታ ህንፃቸዉ አካባቢ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- የኪቶ ፉርዲሳ ካምፓስ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ከሞላ ጎደል የተሟሉ ሲሆን ለመምህራንም ቢሮዎችና ከቢሮ ጋር ተያይዞ ያሉ ፋሲሊቲዎች ተሟልተዋል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት-2፡- 15 የድህረምረቃና የቅ□መ ምረቃ □ሮ□ራሞች (ከዚህ ዉስጥ ሁለቱ በፒኤችዲ ደረጀ) በመክፈት ይከናወናል፡፡

በግማሽ በአመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በነኛ ሩብ አመት አፈፃፀም ሪፖርት ከዕቅድ በላይ 17 የድህረምረቃና የቅድመምረቃ ፕሮግራሞች መከፈቱን ርፖርት ተደርጎ ነበረ፡፡ የተከፈቱት ፕሮግራሞች ሀገሪትዋ ከያዘቸዉ የትራንስፎርሜሽንና ዕድገት አጀንዳ ለማስፈፀም ከሚችሉት ሴክተሮች መካከል ዩንቨርሲቲዉ አንዱ በመሆኑ ይህ ፕሮግራምም ከዚሁ ጋር ተጣጥሞ የተቀረፀ ካርኩለም ነዉ፡፡
- በዚህ ሩብ አመትም፡ በትምህርትና ሙያ መበልፀጊያተቋም ሁለት በPHD(በሦስተኛ ዲግሪ) እና በ MA(ሁለተኛ ዲግሪ) አድስ ፕግራሞችን ለመክፈት ዉይይት ተደርጎ ታስክ ፎርስ ተቋቁሞ የገበያ ጥናት ተጀምሯል፡፡
- በሶሻል ሳይንስና ህግ ኮሌጅ የአራት አዳዲስ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ካሪኩለም ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ ኮሌጅ አድስ የተከፈተዉ <u>የቅድመ ምረቃ ሙዚቃ ትምህርት ክፍል</u> ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይጋኛል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት-3፡- 17 የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ስራዎችን ማከናወን

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታባራት፡-

- የዩኒቨርሲቲው ሌጂስሌሽን ሙሉ ለሙሉ ስራ ላይ ለማዋል የተማሪዎቹ ድርሻ ቢያልቅም የመምህራኑ ድርሻ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- 108 ለሚሆኑ መምህራን የ Instrucctional Skill ስልጠና ተሰጥቷል
- የኢ -ለርኒግ ትምህርት በአንድንድ ኮሌጆች እየተጀመረ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በሶሻል ሶሻል ሳይንስ ህግ ኮሌጅ እንደ አርአያነት ተጀምረዋል፡፡

- አዳዲስ ለተቀጠሩ መምህራን ዩኒቨርስቲውን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ የትምህርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ የመግቢያ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት-4፡- የኢትዮጵየውያን መምህራንን አካዳሚያዊ ማዕረግና የትምህርት ዝግጅታቸዉን ስብጥር ለማሻሻል አሁን ካለው መረጃ፡-

1. ረዳት ምሩቅ አንድ፡- ከ 3.23 ወደ 2.42 በመቶ ዝቅ ማድረግ
2. ረዳት ምሩቅ ሁለት፡- ከ 4.94 ወደ 3.71 በመቶ ዝቅ ማድረግ
3. ረደት ሌክቸረር፡- ከ7.32 ወደ 5.49. ዝቅ ማድረግ
4. ሌክቸረር፡- ከ 54.36 ወደ 56.4 ከፍ ማድረግ □
5. ረደት ፕሮፌሰር፡- ከ26.29 ወደ 27.24 ከፍ ማድረግ
6. ተባባር ፕሮፌሰር ፡- ከ3.01 ወደ 3.60 ከፍ ማድረግ
7. ፕሮፌሰር ፡- ከ 0.56 ወደ 1.14 ማድረስ ነዉ

በትምህርት ዝግጅታቸዉ /ደረጃቸዉ/ አሁን ከለበት፡-

1. የመጀመረያ ዲግሪ፡- ከ15.78 ወደ 12 በመቶ ዝቅ ማድረግ
2. የሁለተኛ ዲግሪ፡- ከ63.77 ወደ 66 በመቶ ከፍ ማድረግ
3. የሦስተኛ ዲግሪ፡- ከ20.45 ወደ 22 በመቶ ከፍ ማድረግ ነዉ



	ረዳት ምሩቅ-I	ረዳት ምሩቅ-II	ረዳት ሌክቸረር	ሌክቸረር	ረዳት ፕሮፌሰር	ተባባር ፕሮፌሰር	ፕሮፌሰር
አሁን ያለበት ደረጃ	3.23	4.94	7.32	54.36	26.29	3.01	0.56
ዕቅድ	2.42	3.71	5.49	56.4	27.24	3.6	1.14
ክንዉን	2.92	4.12	6.51	55.9	26.94	3.05	0.56



	የመጀመሪያ ዲግሪ	የሁለተኛ ዲግሪ	የሦስተኛ ዲግሪ
አሁን የለበት ደረጃ	15.78	63.77	20.45
ዕቅድ	12	66	22
ክንዉን	15.59	63.5	20.91

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ታግባራት፡-

- በሁሉም ኮሌጆች የሁለተኛ ዲግሪ ያለቸዉን ኢትዮጵያዉያን መምህራን ከገበያ ላይ በሌክቸረር ደረጀ ኢንዲቀጠሩ ተደርጎ 129 መምህራን ተቀጥረዋል
- ከዚህ በፊት ለሁለተኛ ዲግሪያቸዉ ወደ ካፍተኛ የትምህርት ማዕካል የሄዱ መምህራን ወደ መደበኛ ሥራቸዉ ስለተመለሱ የሌክቸረር ቁጥር ከፍ ኢንዲል አድረገዋል፡፡
- በሌክቸረር ደረጃ የነበሩ መምህራን በካናወኑት ተጨባጭ ሥራቸዉ ወደ ረደት ፕሮፌሰርነት በማደግ የረደት ፕሮፌሰር ቁጥር እንድጨምር አድረገዋል፡፡
- በተመሳሰይ መልኩ በረደት ፕሮፌሰረነት ማዕረግ ላይ የነበሩ መምህራን ወደ ተባባር ፕሮፌሰረነት በማደገቸዉ የተባባር ፕሮፌሰር ቁጥር ኢንዲጨምር አድርገዋል፡፡
- የሦስተኛ ዲግሪያቸዉን ሲከተተሉ የነበሩ መምህራን ጨርሰዉ ወደ መደበኛ ሥራቸዉ ስለተመለሱ የረደት ፕሮፌሰር ቁጥር በእጅጉ ጨምረዋል
- የሴት መምህራን አስተዋፅኦ ለመጨማር ሁሉም ሴት መምህራን ለብቻቸዉ መኖሪያ እንድኖራቸዉ ተደርገዋል፡፡

ይሁን እንጅ የአካዳሚክ ስብጥሩን በተፈለገዉ ደረጃ ለማድረስ በተለይ የቴክኖሎጅ እና የቢዚነስ መምህራንን በሥራ ላይ ማቆየት ከባድ የቤት ሥራ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

የተጠቀሰዉትን ችግሮች ለመፍታት ደግሞ ዩኒቨርሲቲዉ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ዕጥረት በሚታይባቸዉ የትምህርት መስክ ከዉጪ ሀገረ መምህራንን በመቅጠር በወቅቱ ያለዉን ችግር እየፈተ ይጋኛል፡፡ በዚህ ግማሽ አመትም በተለያዩ ሙያ የሰለጠኑ 17 የዉጪ ሀገር መምህራን በመቅጠር የመማር መስተማር ሥራ ሂደት እንዳይሰተጓጎል ተደርገዋል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 5፡- ያደገ የሴት ተማሪዎች የመመረቂያ ምጣኔ በመቶኛ 88 በመቶ ማስመዝገብ ነው፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ታግባራት፡-

የሴት ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ ቆጥተታና የመመረቂያ ምጣኔያቸውን ከፍ ለማድረግ

- ጥሩ ውጤት ላስመዘገቡ በቁጠር 402 ለሚሆኑ ሴት ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት ተከርክተውላቸዋል፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ላይ ያላቸው አቃም እንዲጠናከር የግንዛቤ ማስጨበጫ ምክር በዩኒቨርስቲው የበላይ አመራርና የሴት ጉዳይ ቢሮ በኩል ተሰጥቷል፡፡
  - የስርዓተ ፆታ ግንዛቤና የተለያዩ ስልጠናዎች ለሴት ተማሪዎች በሁለት ዙር ተሰጥቷቸዋል፡፡
  - በተለያዩ አርዕስቶች ዙሪያ ተከታታይ የሆነ የምክር አገልግሎት በተለይ ለህክምና ተማሪዎች ተደርጓል፡፡
  - ዘግይተው ለገቡ አዲስ ገቢ ሴት ተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫና ከዩኒቨርስቲው ህግና ደንብ ጋር እንዲተዋወቁ የማስተዋወቅ ሥራ ተሰረተዋል፡፡፡
  - ለ364 ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ለሚሹ ሴት ተማሪዎች በየወሩ የገንዘብ ድጋፍ እየተሰጣቸው ሲሆን ለ585 ሴት ተማሪዎች ደግሞ የማቴሪያል ድጋፍ ከሴቶች ጉዳይ ቢሮ ያገኛሉ፡፡
  - ለሴት ተማሪዎች ተጨማሪ የትምህርት ድጋፍ ለመስጠት ሲባል በመኝታቤታቸው አካባቢ አንድ ቤተመጽሐፍትና አንድ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጥ የኮሚፒውተር ላብራቶሪ ተከፈቷል፡፡
  - ፍቃደኛ በሆኑ መምህራን ለነኛ ዓመት የሴት ተማሪዎች የማጠናከሪያ /ቲቶሪያል/ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - በመሪነት ደረጃ የሴቶችን አስተዋፅኦ ከፍ ለማድረግ ሴት ተማሪዎቻችን ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀዉ ሲወጡ ጠንካራና ጥሩ መረ እንዲሆኑ ለማድረግ ከወዲሁ ማብቃቱ አማረጭ የሌለዉ መንገድ ስለሆነ የዩኒቨርሲቲዉ ሴቶች ጉደይ ቢሮ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ለ50 ሴት ተማሪዎች የሊደርሽፕ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርግዋል፡፡

  - የሴት ተማሪዎቻችን ግዜ፤ ገንዘብ እንዲሁም ደህንነተቸዉን ለመጠበቅ በተለይ በኪቶ ፉርዲሳ ካምፓስ ከከተማ የሚያገኙትን አገልግሎት እዛዉ ጊቢ ዉስጥ ማግኘት እንድችሉ የሴቶች ዉበት ሳሎን በግቢዉ ዉስጥ ተከፍቶላቸዉ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት እየሰጠ ይጋኛል፡፡

  - በስርዓተ ፆታ ላይ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ በዩኒቨርስቲው ዉስጥ በሁለት ዙረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፎረም ተከፍቶ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ለሴት ተማሪዎቻችን አስፈላጊዉ ስልጣናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰረተዋል፡፡

  - ሴት ተማሪዎቻችን በተለያዩ ማህብራዊና ጤና ነክ ጉደዮች ላይ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ በሴቶች ጉደይ ቢሮ ተከታታይ የምክር አገልግሎቶች እየተሰጠቸዉ ይገኛል፡፡

- ሴት ተማሪዎቻችን ላይ ፆታዊ ትንኮሳ እንዳይደርስባቸዉ ለመከላከል በዋናዉ ግብም ሆነ በሀሉም ኮሌጆችና ከምፓሶች ትንኮሳን የሚከላከል ወይም ያለዉን ጉደይ ለሚመለከተዉ አካል የሚያሰዉቅ ከተማሪዎቹ ዉስጥ ከሁለቱም ፆታ የተዋጣጡ ኮሚቴዎች ተቃቅሞ በስራ ላይ ይጋኛል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት-6፡- በኤችአይቪ ኤድስ፡ ልዩ ድጋፍ፡ ና መሰል ጉዳዮች ላይ በተሰጡ አገልግሎት የተገኘ ውጤቶች

- ስለኤች አይቪ/ኤድስ የተሟላ ግንዛቤና ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች ድርሻ ከመቶ ወደ 90 ይደርሳል፡፡
- ቫይረሱን በመከላከል ረገድ በጎ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ድርሻ ከመቶ ወደ 75 ይደርሳል፡፡
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ከአንድ በላይ ጓደኛ ያላቸው ተማሪዎች ድርሻ ከመቶ ወደ 14.2 ይወርዳል፡፡
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ከአንድ በላይ ጓደኛ ያላቸው ተማሪዎች ድርሻ ከመቶ ወደ 14.2 ይወርዳል
- በሱስ የተጠመዱ ተማሪዎች ድርሻ ከመቶ ወደ 10.05 ይወርዳል
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረስጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ተማሪዎች ድርሻ ከመቶ ወደ 12.9 ይወርዳል፡፡
- ለአካል ጉዳተኞች ተጨማሪ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

የአለም የኤድስ ቀን በዩኒቨርስቲው ሲከበር የሚከተሉትን አኩሪ ተግባራትን አከናዉነዋል፡፡□

- በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በተደረገዉ ክበረ በዓል ላይ ከተለያዩ ክፍሎች (ከዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ፤ ከከተማዉ ነዋሪ ፤ ከመጀመሪያ ደረጀ ትምህርት ቤቶች የመጡ የነገ ተስፋ ተማሪዎች እና የዩኒቫርቲዉ የበላይ አመራሮች በተገኙበት) በፕሮጀክቱ አሰተባባር ተወካይ አለም አቀፋዊ ልምዶችን ያጠቀሰ የግንዘቤ ማስጨበጫና ትምህርት አዘል ሪፖርት ቀርቦ ዉይይት ተደረጎበታል፡፡ በተጨማሪም የፓናል ዉይይት በዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ መካካል ተደርጎ ካፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሰርተዋል፡፡
- በዋናው ጊቢ በተደረገው ክብረ በዓል ላይም ተማሪዎች ፤መምህራንና ሠራተኞች የተሳተፉበት በተለያዩ የስፖርት ውድድሮች የታጀበ የግንዛቤ ማስጨበጫ ኘሮግራም ተካሂዷል፡፡
- ከ5000 በላይ የሚሆኑ ስለኤችአይቪ ጥሩ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ብሮሸሮች ፤ፖስተሮችና ፖምኘሌቶች በማዘጋጀት ከበዓሉ በፊትና በኋላ የህዝብ ማዕከል በሆኑ ቦታዎች ላይ ከማለጠፍ በተጨማሪ ለግለሰቦችም እንዲሰራጭ ተደርገዋል፡፡
- ከኤችአይቪ ኤድስ ዙሪያ 12 የስልጠና ኘሮግራሞች ለህብረተሰቡ ለመስጠት ታቅደዉ አምስት የስልጠና ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዉ ለዩኒቨርሲቲዉ ሴት መምህራንና ተማሪዎች ተሰጥተዋል፡፡
- በአመቱ 20 አውደ ጥናቶች በዓመቱ ለማስከድ ታቅደው 8 አውደ ጥናቶች በዚህ ግማሽ ዓመት ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

- የኤችአይቪ ኤድስን ሂደት በዩኒቨርቲው ቅጥር ጊቢ ውስጥ ብቻ መግታት ስለማይቻል ወደ ማህብረሰቡ መግባትም አስገደጅ ጉደይ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲዉ ኤችአይቭ ኤድስ መከላካያና መቆጣጠሪያ ፕሮጄክት ከጂማ ከተማ ወጣቶች ጋር ለመስራት በስምምነት ላይ ተደርስዋል፡፡
- ይህ ፕሮጀክት መሠረታዊ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ለ200 ተማሪዎች በቢሮው በኩል አስፈላጊውን ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡
- ኤች አይቪ ኤድስን በሚመለከት ለከለብ አመራሮች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በተለያዩ ጎጂ ሱሶች የተጠቁ ተማሪዎች ለማገገሚያ የሚሆን ማዕከል እንዲቋቋም ታቅዶ በዚህ ግማሽ ዓመት ለማዕከሉ ማገልገያ የምዉሉ ማቴሪያሎች ተገዝቶ ገብተዋል፡፡ ማዕከሉም በቅርብ ግዜ ሥራዉን ይጀምራል፡፡
- በስድስት ዙር ለአንድሽህ (1,000) ተሳታፍዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፎረሞች በሩብ ዓመቱ ለማከሄድ ታቅዶ ከዕቅድ በላይ ለ1,200 ሰዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተካሂደዋል፡፡
- ድጋፊ ለሚሹ ሴት ተማሪዎችን በቀጥታ ገንዘብ በእጅ በመስጠት መርዳቱ ቀጣይነት ስላሌለዉ ፕሮጀክቱ የተሸለ መንገድ ስያፈላልግ ቆይቶ የወሰደዉ አማራጭ ገቢ ማመንጨት የሚችል አገልግሎት የሚሰጥ ፕሮጀክት ለመቋቀም ታቅደዉ በዚሁ መሠረት አንደ የልብስ ማጠቢያ ማሽን በግቢ ዉስጥ ተቋቅመዋል፡፡ ይህ ማሽን በየግዜዉ በዩኒቨርስቲ ዉስጥ ስለምቆይ በቀጣይነት የተማሪዎችን ችግር ሊፈታ ይችላል፡፡

3.1.2. □ሮ□ራም ሁለት /የትኩረት መስክ፡- ጥናትና ምርምር

ስትራቴጂክ ዓለማ፡- ጥራቱንና አግባብነቱን የጠበቀ፡ ተደራሽነቱ የሰፋ ፍትሃዊ ምርምር በማካሄድና

ለተጠቃሚው በማድረስ የደንበኞችን/ባለድርሻ አካላትን እርካታ፡ አምነትና ጥቅም ማሳደግ

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 1፡- □ኮካሄ□ ብሄራዊና ዓለምአቀፋዊ የጥናትና ምርምር

ጉባኤዎች/ኮንፈረንሶች/ ብዛት (8) ይሆናል

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታጋባራት፡-

- በሁለተኛው ሩብ አመት በምዕራብ ኢትዮጵያ ካሉ ዩንቨርስቲዎች ማለትም ጅማ፤አሶሳ፤ወሊጋና መቱ ለተውጣጡ 490 ለሚሆኑ ተሳታፊዎቸ 'Teal and Agora Train the Trainer Workshop' በጅማ ዩንቨርስቲ አስተባባሪነት ተካሂዷል
- በሁለተኛው ሩብ 36 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች የሁለት ቀን ዎርክ ሾፕ በ sustainable indiginious bio fertilizer ላይ ተካሂዷል
- በሁለተኛው ሩብ 70 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች ከBrown University ጋር በመተባበር Reproductive Health በሚመለከት ዎርክ ሾፕ ተካሂዷል
- ለግማሽ ዓመቱ ከታቀደው በላይ ነ0 ብሄራዊ እና ዓለምአቀፋዊ የጥናትና ምርምር ጉባኤዎች/ ኮንፈረንሶች ተካሂዷል፡፡
- ለአምስተኛው ዓመታዊ ጉባኤ/ኮንፈረንስ የሚሆኑ ግብዓቶች ፤ ምርምሮች/የመረጃ ማሰባሰብ ስራዎች ደረጃ በደረጃ እየ ተ ከ ና ወኑ ይገ ኛ ሉ፡ ፡
- ለግማሽ ዓመቱ ሦስት ኘሮፖዛሎች ተዘጋጅቶ ለተባባሪዎች ቀርበዋል፡፡ ይህም ለግማሽ ዓመቱ ከታቀደዉ በላይ በአንድ ብልጫ በማሳየት ከዕቅድ በላይ ተከናዉነዋል፡፡
- በየኮሌጆቹ መምህራንና የማስተርስ ተማሪዎች የምርምር ስራ በቴማቲክ ኢንዲሆን ተደርጎ ዋና ተመራማር ከመምህራን የሚመደብ ሲሆን ተማሪዎቹ በዚህ ስር እንድደረጁ ተደርጎ አፈፃፀሙ በዘሁ መልኩ ተካሂዷል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት2፡- በአለም አቀፍ ደረጃ□እዉቅና ባላቸዉ ጆርናሎች ላይ □ታተሙ

የምርምር ዉጤቶች ብዛት (150) ይሆናል፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- የተማሪዎች የጥናትና ምርምር ዉጤቶች በተዋቂ ጆርናሎች ላይ ለማሳተም በሂደት ላይ ይጋኛል፡፡
- ***120 የምርምር ዉጤቶች አለም አቀፋዊ ዕዉቅና ባለቸዉ ጆርናሎች ላይ □ታትመዋል፡፡***

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት3፡- የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን ጨምሮ ተገምግሞ ፈንድ የተደረጉ የምርምር ፕሮፖዝሎች ብዛት 660 ይሆናል፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

ምስል ቁጥር-2



የክንዉን መግለጫ

- 22 ምርምሮች በዚህ ግማሽ አመት ተሰርቶ ተጠናቀዋል
- 280 የሚሆኑ የመምህራን የምርምር ፕሮፖዝሎች ለፈንድ ብቁ እነዲሆኑ በየኮሌጃቸዉ ግምገማ እየተደረገለቸዉ ይጋኛል፡፡
- 12 የምሆኑ ቀጣይነት ያላቸዉ የምርምር ስራዎች በሀይል ማመንጫ፤በማዳበሪያ፤ በጤና፤በግብርናና አካባቢ ጥበቃ፤ ንፅህና፤በምግብና ህክምና እንዲሁም ሌሎችም በምርምር የሥራ ሂደት ዉስጥ ይጋኛሉ፡፡
- 115 የምርምር ንደፈ ሃሳቦች ከድህረ ምረቃ ተማሪዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከዚህ ዉስጥ በቴክኖሎጂ ላይ የተሰሩ ሲሆን እነሱም፡-
    - በመንገድ ስራ ከ70 በላይ የሚሆኑ
    - በኢነርጂ ረገድ ከ12 በላይ የሚሆኑ
    - በኮሚኒኬሽን ከ 3 በላይ የሚሆኑ
    - በውሃ እና በአካባቢ ከ10 በላይ የሚሆኑ ችግር ፈቺ ጥናቶችን እያከናወነ ሲሆን በአሁኑ ሰዓትም ከሴክተሮች ድጋፍ በማግኘት ላይ እንገኛለን፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት4፡- ከሌሎች ባለድርሻ አካላት በተገኘ ድጋፍ/በጋራ ትብብር አዲስ የሚጀመሩ ምርምሮች ብዛት/ 7/

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ታግባራት፡-

- በግማሽ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም ውስጥ ዩኒቨርሲቲዉ በደረገዉ የድገፊ ማፈላለግ ስራ ከ USAID ጋ ር ወባ ን ለ መከ ላ ከ ል የ ሚያ ስ ችል ፈ ን ድ ተ ፈ ራ ር ሟል
- የሚገኙ የምርምር ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስችል ለግማሽ ዓመቱ አንድ ኘሮፖዛል ለማዘጋጀት ታቅደው ከዕቅድ በላይ ሦስት /3/ ኘሮፖዛሎች ተዘጋጅተው ለባለድርሻ አካላት ተልከው ሁለቱ ተቀባይነት ሲያገኙ የአንዱን ውጤት ግን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡□
- አንድ ፈንድ የሚያስገኝ ፕሮጀክት ተቀርፆ ለከነስቴል ፋዉንደሽን ቀርቦ ፕሮጀክቱን በማሸነፍ በተገኘዉ ፋንድ በጂማ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ለ404 ቤተሰቦች በምግብ ራሳቸዉን እንዲችሉ የሚያግዝ ፕሮጀክት ተጀምሯል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት5፡- ለህብረተሰቡ/ ለተ□ ቃሚዉ □ዙላለ□ □ምርምር ዩ ጤቶችና ስራ ላይ የዋሉ ብዛት (7) ይሆናል፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በጅማ ዞን በሸቤና ሰርቦ ወረዳ ሁለት የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኘሮጀክቶች ግንባታ ስራ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውሉ ተደርገው እየተካሄዱ ነው፣
- በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እያንዳንዱ የምህንድስና የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ ከመመረቁ በፊት አንድ ፕሮቶ ታይፕ ከመምህሩ ጋር በመሆን ማዘጋጀት ስለሚጠበቅበት ኢንዱስትሪውን ሊያግዙ የሚችሉ የተለያዩ ዲዛይኖችን እና ፕሮቶ ታይፖችን አዘጋጅተን ወደታች ለማውረድ በእንቅስቃሴ ላይ ስንሆን ይህንን ሲስተም ዘርግተን ለማከናወንም ከጀርመን መንግስት GIZ በኩል አንድ አማካሪ እንዲመደብልን ጠይቀን በአሁኑ ሰዓትም አማካሪውን ለማግኘት የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንገኛለን፡፡
- RELOAD ከተሰኘው ፕሮጀክት ከ 4 የጀርመን እና ከ 5 የ አፍሪካ አገር ዩኒቨርሲቲ እና ተቋማት ጋር የምርምር ስራ እዲጀመር ተደርጓል .
- በጅማ ዞን በሸቤና ሰርቦ ወረዳ ሁለት የሃይድሮ ኤለክትሪክ ኘሮጀክቶች ግንባታ ስራ ለህብረተሰቡ አገልግሎት
- እንዲውሉ ለማድረግ አንዱ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን ሁለተኛው ግን ዝርዝር ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ግንባታ በመሸጋገር ላይ ነው፡፡
- በግልገል ጊቤ የመስክ ምርምር ማዕከል የተሰበሰቡና የተቀናጁ የሰርቪላንስ መረጃዎችን ለተጠቃሚውና ለሚመለከታቸው አካላት ተሰራጭተዋል፡፡
-
- RELOAD ከተሰኘው ኘሮጀክት ከ4 የጀርመን እና ከ5 አፍሪካ አገር ዩኒቨርስቲ እና ተቋማት ጋር የህብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የምርምር ስራ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡

በአመቱ መጨረሻ ሚጠበቅ ዉጤት 6፡- □□ቀው፡ ስራ ላ□ □□ሉ ተጨማሪ የምርምርና ስፀርት መመሪያዎች

የግማሽ አመቱ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በግማሽ ዓመቱ አንድ የምርምርና ስርፀት መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ፀድቀው ለክንውን ለሚመለከተው አካል ተሰራጭቶ በመመሪያዉ መሰረት ስራ ተጀምሯል፡፡
- በአዲሱ የምርምር ሰራ ስርፀት ግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክ ሾፕ ተካሂዷል
- የደህረ ምረቃ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ዩኒቨርስቲው ካዘጋጀው ቴማቲክ (thematic area) ሳይወጡ ምር ምራቸዉን ኢንዲሰሩ የክትትልና ግምገማ ሥራ እየተካሄደ ነዉ። ፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 7፡- የተካሄዱ የአቅም ግንባታ□ ስራዎች

የግማሽ አመቱ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በሩብ ዓመቱ በዩኒቨርስቲው ላይብራሪ ለአን ጊዜ /TEEAL AND AGORA / ላይ የአስልጣኞች ስልጣና ተሰጥቷል፡፡
- የባዩ ቴክኖሎጅ ኢኒስቲትዩት በዚሁ ግማሽ ግመት ውስጥ ተመሰርተው ሥራ የጀመረ ሲሆን ይህ ኢኒስቲትዩት አራት ማዕከሎችን ያቀፈ ነው፡ □እናሱም፡- center for Myco –Bacteriology, center for natural and pharmaciticuals molecular biology and center for plant and animal biotechnology ናቸዉ፡፡
- ለ32 ተሳታፊዎች በሪሰርችና ፕብልኬሽን ላይ የ ኮንሰልታቲቭ ዎርክ ሾፕ ተካሂዷል
- 48 ለሚሆኑየዩንቫርሲቲዉ መምህራን ከILRI ጋር በመተባበር በ Grant Proposal Writing ላይ መሠረታዊ ስልጠና ተሰጥቷል
- 120 ለሚሆኑ ከቡሬ ሆራ፤ከሙቱና ከአሶሳ ዩንቨርስቲ ዎች ለተውጣጡ ተሳታፊዎች በ Grant Proposal Writing and Data Handling ላይ ስልጠና ተሰጥቷል
- የምርምርን ክህሎት ከፍ ለማድረግ 30 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች በ Qualitative Research ላይ ስልጠና ተሰጥቷል
- በተጨማሪም የመምህራኑን የምርምር አቅም ለማጎልበት በህብረተሰብ ጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ በResearch Stastical Methods ,በClinical Research ,በMeta-Analysis Certification እና Research Grant Writing ላይ አጫጭር ስልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡
- በህብረተሰብ ጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ በቬለር ፕሮጀክት በHolticultural Linear Modeling Systematic Review እና Grant Writing ላይ የአጭር ጊዜ ስልጠና ተሰጥቷል፡
- ለአምስት ቀናት ያህል ከ Ohio State University, በመጡት Professor Ann O' Connell, ለ55 በለሙያዎች በ-Specialized Higher Statistical Course on Hierarchical Linear Modeling ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥተዋል፡፡
- በሳይንትፍክ ራይትንግ ላይ ለ25 የድህረምራቃ ተማሪዎችና የአካደሚክ ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥተዋል፡፡

3.1.3. □ሮ□ራም ሦስት /የትኩረት መስክ፡- የማማከርና የሕብረተሰብ አገልግሎት

ስትራተጂክ ዓለማ፡- ጥራቱንና አግባብነቱን የጠበቀ፡ ተደራሽነቱ የሰፋና ፍትሃዊ የማማከርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ለተጠቃሚው በመስጠት የደንበኞችን/ባለድርሻ አካላትን እርካታ፡ አምነትና ጥቅም ማሳደግ

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 1፡- በዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል በተሻሻሉ የተኙቶ መተከም፡ ተመላላሽ ህክምና፡ ድንገተኛና የማዋለድ እንዲሁም የደርሶ መልስ አገልግሎቶች □□ተ□ለ□ሉ □ታካሚዎች ብዛት (250000)

ምስል ቁጥር-3



የሁለተኛዉ ሩብ አመት አፈፃፀም ከአንደኛዉ ሩብ አመት ስናፃፀር በ2.6 በመቶ እየጨመረ መሄዱን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ በቀጣዩ የሥራ ግዜያት ጥሩ የአግልግሎት ማስጫ እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- ሆስ□ታሉን በሰዉ ሀይል ለማሟላትና ተጨባጭ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማስጠት በተለ□□ የሙያ መስክ የሠለጠኑ በለሙያዎችና የአስተደደር ሠራተኞች በጥቅሉ 13 ሠራተኞች ተቀጥሯል።
- □ሆስ□ታሉን አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በቁ□ር ስ□ስት (6) ሰራተኞች በተለያዬ የጤና ነክ ጉዳዮች ላይ በህንድ ሀገር ስልጠና እንደወሰዱ ተደርገዋል።
- ሆስ□ታሉን በተለያዬ ግብ□ትና አገልግሎቶች ለማሟላት በታቀ□ መሰረት ተከናዉኗል።

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት2፡- □ተሻሻሉ □ሆስ□ታል አገልግሎቶች ብዛት (4)

- ተመላላሽ ታካሚዎች ህክምና እስኪያገኙ ቆይታ ከ60 ደቂቃ ወደ 50 ደቂቃ ማውረድ
- □መሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦት አማካይ የስቶክ ዕጥረት የቆይታ ጊዜን ከ ሁለት ቀን ወደ አንድ ቀን ማውረድ
- የሞት ምጣኔን መቀነስ
    - ተኝቶ ታካሚዎች ከ1.26 ወደ 1.0 ማውረድ
    - ኢመርጀንሲ ሩም 0.075 ላይ ማቆየት
    - ማተርናል ከ0.39 ወደ 0.1 ማውረድ
- የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ማሻሻያ መርሃግብር መሰረት ስራ ላይ የዋሉ ስታንዳርዶች ድርሻ በመቶኛ (80)
- የተጠናከሩን አዲስ የተጀመሩ □ሆስ□ታል አገልግሎቶች ብዛት ዘጠኝ ይሆናል

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በግማሽ አመቱ 102 ለሚሆኑ የአከባቢዉ አካል ጉዳተኞች የአርቲፊሻል ፕላስቲክ የአካል ደጋፊ በሆስፒታሉ ፒኦሲ ክፍል ተመርተዉ ለአካል ጉዳተኞች ተሰረጭቷል።
- የአካል ጉደተኞቹ ማዕከል ይህንን የአርተፍሻል ፕላስቲክ በማምረት በጂማ ዞን ኢንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልለዊ መንግስት ዉስጥ ለሚገኙት ለአቅረቢያ ህብረተሰብ ይህ አገልግሎት እየተሰጠቸዉ ይጋኛል።
- በ **ሁለተኛ ሩብ** አመት አንድ ሰፔሻል ክሊኒክ (Opretive and endodontics and maxillofacial room) ተከፍቷል።
- ከ German MLU ጋር በመተባበር በ Estabilishment of medical schools in low resource setting ላይ ደብረ ዘይት ስልጠና ተሰጥቷል
- በ **ሁለተኛ ሩብ** አመት ከናይጀሪያ ዩንቨርስቲ ሆስፒታል ጋር በመሆን በጤና -ኮሚኒኬሽንን አቅም ግንባታ ላይ ስልጠናና የልምድ ልዉዉጥተደርጓል
- **የአዲሱ ሆስፒታል ግንባታ□ ማጠናቀቅ፡ የህክምና መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች መሟላትአስፈላጊዉ** ስራ በመሰራት ላይ ነው።

- በሆስፒታሉ ላይ መዋቅራዊ ማሻሻያ እንዲደረግ ታቅደዉ በዚሁ መሠረት የማሻሻያ ሂደቱ ወደ መጨረሻዉ ምዕራፍ ላይ ይጋኛል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት3፡- በተማራ- ች የመስክ ስልጠና ፕሮግራም አገልግሎት ያገኙ ተጠቃሚዎች ብዛት (600000)

ምስል ቁጥር-4



በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- **በ □ማሽ □መቱ ተማሪዎች በሲቪቲፒ፡ ቲቲፒ፡ ኢንተርንሽፕ፡ ፕራክቲከምና ፕሮፌሽናል ፕራክቲስ ተሳታፊ ሲሆን ለተማሪዎቹ ስምሪት ግብኣት የማሟላትና የትራንስፖርተሽን አገልግሎት አቅርቦት ሙሉ ለሙሉ ተከናዉኗል፡፡**
- **በ □ማሽ ዓመት የሥራ አፈፃፀም በተለያዩ የተማሪዎች የመስክ ስልጠና ፕሮግራም አገልግሎት ያገኙ ተጠቃሚዎች ብዛት 240000ናቸዉ፡፡**

- **በሁሉም ኮሌጆች የሚገኙ የድህረምረቃ ተማሪዎች በሚያደርጉት በዲቭሎፕሜንት ትሬንግ ፕሮግራም ለጂማ ከተማና አከባቢዋ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ፤ ሽንት ቤቶች፤ ድልድዮች፤ የቤተሙከራና ቤተመፅሐፍት መደራጀት ፤** □እንድሁም በተመሳሳይ መልኩ ህብረተሰብ አቀፉ አገልግሎቶችን ስያከናዉኑ ቆይተዋል፡፡
- **በተፈጥሮ ሳይንስ የድህረምረቃ ተማሪዎች ለድል ፍሬ ትምህርት ቤት የሚተላ የሣይንስ ቤተ ሙከራ አደረጅቷል፡፡**
- **በተመሳሳይ መልኩ ለሦስት ትምህርትቤቶችም ቤተመ□ሐ□ታቸዉን** በመፅሐፍ የማደረጃት ሥራ ተሰርቷል፡፡
- **በዚሁ ድል ፍሬ ትምህርት ቤት አንድ የአይ ሲቲ ማዕከል በ 15 ኮምፒዉተሮች፤ በ15 ወንበሮች የተደረጁ ሲሆን የኔትዎርክ ቁሳቁሶችም ተደረጅቷል፡፡**
- **በሰ□ ሰመሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአ**ካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ምቹ የመማሪያ አከባቢ ለመፍጠር የመፀደጃ ቤትና የዉስጥለዉስጥ የጥርጊያ መንገድ ተሠረቷል፡፡
- **ወንበርና ጠረጴዛ ላሌላቸዉ የማዋለ ህፃናት** ትምህርት ቤት **ደረጃቸዉን የጠበቁ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች** ለግሷል፡፡
- ጥቃቅን ከውሃ የሚመነጭ የሐይል አቅርቦት (Micro Hydro Power) በአሁኑ ሰዓት በጅማ ዙሪያ በቀርሳ ወረዳ ከ AIPHA SOL ጋር በመሆን የስራውን የገንዘብ መጠን 15% ዩኒቨርስቲው በመሸፈን ከ 650 በላይ ነዋሪን እና የተለያዩ ተቋማትን የኃይል አቅርቦት ሊሸፍን የሚችል የኤሌክትሪፊኬሽን ስራ ከ90% በላይ በማጠናቀቅ በአሁኑ ሰዓትም ተጨማሪ የሀልይ አቅርቦት በሸቤ ሰምቦ ወረዳ ለኩ ሳይት ከGIZ እና ከኦሮሚያ ውሃ ቢሮ ጋር በመሆን ከ 13KW በላይ የሚያመነጭ ስራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡
- ከ TVET ጋር ያለው ግንኙነት- ዩኒቨርስቲያችን "We are in the Community" ብለን እየሰራንበት ባለው አቅጣጫ መሠረት የጂማ ዩኒቨርሲቲ ኢንስቲትዩት ከአምስት ክልል (ከጋምቤላ፣ ኦሮሚያ ፣ ቤንሻንጉል፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች፣ እንዲሁም ከአዲስ አበባ) እና በውጭ ሐገር ከሚገኙ (ከደቡብ አፍሪካ፣ጀርመን፣ሞዛቢክ እና ከአሜሪካ)የተለያዩ ተቋማት ጋር በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም MoU ተፈራርሞ ወደ ተግባር ተገብቶአል ለምሳሌ ያህል ከ20 በላይ ለሆኑ ከ TVET ተቋማት ለመጡ መምህራን የ Auto Cad ስልጠና እንዲያገኙ፣ ተማሪዎቹ በውጭ ሀገር የተሰሩ ፕሮቶታይፖችን እንዲቀስሙ፣ በኢንስቲትዩታችን የሚገኙ Proto Type እና ዲዛይኖችን ደግሞ ሰፊ ማብራሪያ ለ TVET በመስጠት ወደ ታች አውርደው እንዲተገብሩ ስራዎች እየሰራን እንገኛለን፡፡
- የሕብረተሰብ አቀፍ ትምህርት የዩኒቨርስቲያችን ፍልስፍና እንደመሆኑ በዚህም ዙሪያ ተማሪዎቻችን፣ መምህራኑን እና ኢንዱስትሪውን ሊያስተሳስር የማችሉ ስራዎች ተከናውኖአል፡፡ ለምሳሌ 1.2 ማሊዮን ብር ሊያወጣ የሚችል የመንገድ ስራ ከጅማ መንገዶች ባለስልጣን እና ከሌሎች ሴክተሮች ጋር በመሆን በከተማችን ከጥቅምት እስከ ህዳር በ DTTP አከናውነናል፡፡
- የተለያዩ የላቦራቶሪ (Construction Material Testing, Highway Material Testing, soil Testing) ግልጋሎቶችን ለማንባታው እና ለመንገድ ሴክተር ሰጥተናል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 4፡- ለተቃማትና ማህበረሰብ የተሰጡ ሌሎች አገልግሎቶች

ብዛት 58 ሲሆን ከዚህ ዉስጥ፡-

- የማማከር አገልግሎት 12
- በፍላጎት ላይ ያተኮረ ስልጠና 21
- ሌሎች ድጋፎች 25

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

በተለያዩ የዩንቨርሲቲዉ ሥራ ክፍሎች / ኮሌጆች ለማህበረሰቡ የተሰጡ አገልግሎቶች

- **በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በኩል የተለያዩ ምርጥ ዘሮች ለተጠቃሚዉ ለአከባቢው ህብረተሰቡ ተላልፏል፡፡**
- **ከ 1790 በላይ ለሚሆኑት ለአከባቢዉ እንስሳት የህክምና አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡**
- የግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ለአካባቢዉ ማህበረሰብ በግብርና ኤክስቴንሽን ለይ አስፋላጊዉን ስልጠና ሰጥተዋል፡
- በጅማ ከተማ በዝቅተኛ ኑሮ የሚተዳደሩ ሴተኛ አዳሪዎች ከኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ ጋር አብረው የሚኖሩ ወገኖችናለስራአጥ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን ማዕከል ላደረጉ የጥቃቅንና መካከለኛ ገቢ ማመንጫ ማህበራት የክህሎት ማበልፀጊያና ለመሬት ዝግጅት የትራክተር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- **የጋራ መድረኮችን ማመቻቸትና መጠቀም ረገድ የጂማ ከተማ ልማት አማካሪ ፎረም ላይ ንቁ ተሳትፎ ከማድረግ ጎን ለጎን ለኮሚቴዉ የማስሪያ ቢሮ ተከራይተዋል፡፡በተጨማሪም የጅማን ከተማ በማስዋቢ ዙሪያ ዩንቫርሲቲዉ የተለያዩ ተክሎችን በማስጣት፤ የሣር ማጨጃ ማሽን በማወስ እንዲሁም የመማከር አገልግሎቶችን በማስጠት ሳፊዉን ድርሻ ተጫዉተዋል፡፡**
- **የልማት አማከሪዉ ፎረም ከጅማ ከተማ መስተዳድር ጋር ለመስራት በዚህ ግማሽ አመት ዉስጥ የጋራ እቅድ በማዘገጀት ወደ ተጨባጭ ሥራ ለማግበት በዝግጅት ላይ ነዉ፡፡**
- የጂማ ከተማ ችግር ፈች ኮሚቴ በዩንቨርሲቲዉ ዉስጥ ተቃቁሞ በከተማዉ ችግሮች ዙሪያ ሰፊ ምክክሮችን በማከሂድ ላይ ይገኛል፡፡
- የጂማ ዩንቨርሲቲ ፈጠራ የሆነዉን Hay Box የጫጩት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂ 20 Hay Box ተዘጋጂቶለዲላ ዩኒቨርሲቲ በኪፍያ እንዲወስዱ ተደርጎዋል፡፡

- **በጂማ ዩኒቨርሲቲአብያተመፅሃፍት 720 የተለየዩ ሶፍት ኮፒ መፅሓፎች በድጋፍ ለፀማ** ከተማና አካባቢዋ ለማገኙትምህርት ቤቶች □ፉ□ ተ□ርጿል
- በ ግማሽ ዓመት DTTP ፕሮግራም በ ቦሳ አዲስ ቀበሌ፤በቦሳ ኪቶ፤ስጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በዲል ፍሬ ት/ቤቶች communal latrine ግንባታ ተካሂዷል፡፡እንድሁም ቦሳ አዲስ ቀበሌ፤በቦሳ ኪቶ ቀበሌዎችና ትምህርት ቤቶች በህዝብ ሽንት ቤቶች የመታጠቢያ ዉሃ ተሰርቷል፡፡
- በ ግማሽ ዓመት በDTTP **ፕሮግራም ለአካባቢዉ 1 ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች** የቤተ መፅሃፍት ማደራጀት፤የሳይንስ ቤተ ሙከራን ማደራጀት፤የልዩ ትምህርት ማዕከልን መክፈትና የ አይሲቲና ኔት ዎርክ ዝርጋታና የቁሳቁስ እርዳታ ለትምህርት ቤቶቹ ተደርጓል
- በሳይኮሎጅ ትምህርት ክፍል ነፃ የምክር አገልግሎት ማዕከል ለመክፈትና ነፃ የካዉንስሊንግ አገልግሎት ለመስጠት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል
- በ **ሁለተኛ ሩብ አመት** በትምህርትና ሙያ ማበልፀጊያ ጥናት ተቋም አማካኝነት 500 ለሚሆኑ ከ 5 ማዕከላት ለመጡ የወረዳና የት/ቤት ሱፐርቫይዘሮችና አለቆች ሥልጠና ተሰጥቷል
- 35 ለሚሆኑ የ10 ኛና 12 ኛ ክፍል እንግሊዘኛ መምህራን TEFL ስልጠና በ ELIP ተጠሰጥቷል፡፡

በዩንቫርሲቲዉ ኣይ ሲቲ (ICT) ለእህት ዩንቨርሲቲዎች የተሰጡ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት፡

- ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲት ሙሉ የኔትወርክ ዝርጋታ ስራ ተጀመሯል እንዲሁም ለ 6 ባለሙያዎች የአቅም መገንባት ስልጠና ተሰቷል፡፡
- ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲት- ሙሉ የኔትወርክ ዝርጋታ አግሪመንት ተፈርሟል
- ለቡሌ ሆራ ዩንቨርስቲ ኔትዎርክ ዝርጋታና የቢሮ ዕቃዎች ተከላና ጥገና ስልጠናና የአቅም ግንባታ ድጋፎች ተደረገዋል
- ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲት ሙሉ የኔትወርክና ፋይበር ዝርጋታ ስራተጠናቆ በተጨማሪም ለ6 ባለሙያዎች የሙያ መበልፀግያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- አራት የሃረማያ ዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎች የክሕሎት ማደበሪያ ስልጠና ወስደዋል
- የሃሮማያ ዩኒቨርሲት አራት ባለሙያዎች በኣይሲቲ ዙሪያ አግባብ ያለዉ ስልጠና ወስደዋል

- የመቱ ዩኒቨርሲትየኔትወርክ ዝርጋታና የኮንፊግሬሽንና ዳታ ሴንተር ማደራጀት ተጠናቆ ለዩንቨርስቲዉ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለዩንቨርስቲዉ ባለሙያዎች በሃርድ ዌር ሜንቴናንስና ትራቨል ሹቲንግ ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል
- ለመቱ ዩኒቨርሲት የኔትወርክ ዝርጋታው ተጠናቆ የኮንፊግሬሽንና ዳታ ሴንተር ማደራጀት ብቻ ይቀራል፡፡
- ከሰመራ ዩንቨርስቲ ጋር ሁለተኛ ዙር የኔትወርክ ዝርጋታ ስራ አግሪመንት ተፈርሞ ወደ ስራ ለማግበት በዩኒቨርስቲዉ በኩል ባሉ አንዳንድ ችግሮች ወደ ስራ መግባት አልተቻለም
- ለአምቦ ዩኒቨርሲት- ለ ምግብ ቤት ፡ ለ ጥበቃ ና ደህንነት ፡ ለሊይብራሪ ሎን ሲስታም ፡ ለመኝታ አገለግሎት የሚዉል one card system ስራ ተሰርቶዋል፡፡
- ለአምቦ ዩኒቨርሲት - one card system ለ ምግብ ቤት ፡ ለ ጥበቃ ና ደህንነት ፡ ለሊይብራሪ ሎን ሲስታም ፡ ለመኝታ አገለግሎት ስራ የሚዉል ሶፍትዌር ተዘገጂቶ ተሰርቶዋል፡፡
- ከአርዳታ ቲቪት ኮሌጅ ጋር የስራ አግሪመንት ተፈርሟል

ዩኒቨርሲቲዉ ከዉጪ ሀገር በአካደሚያዊ የጋራ ትብብር አብሮ ለመስራት ከተፈራረመባቸዉ ፕሮጀክቶች ጋር በመሆን ለአከባቢዉ ማህብረሰብ የተሰጡ አገልግሎቶች

በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በሚገኘዉ ከ “Ethio-Netherlands CASCAPE Project” ጋር የተሰሩ ተጨባጭ ስራዎች፡-

- በጅማ ዞን በጌራ፣ በኦሞናዳ እና በሊሙ ሰቃ እንዲሁም በኢሉባቦር ዞን በበደሌ እና በዲደሣ ከእያንዳንዱ ወረዳ አራት ቀበሌዎችን በመምረጥ አርሶ አደሩን በማወያየት በአካባቢው ነልተው የሚታዩትን የግብርና ማነቆዎች በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡
- የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን (የአፈር ማዳበሪያ እና የተለያዩ ምርጥ ዘሮች) በተፈለገው ቦታ በማድረስ፣ በተለዩ ስነ ምህዳሮች የተሻሻሉ የተመሰከረላቸው ምርጥ ዘሮች በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ የቴክኖሎጅ ስርፀት እያካሄደ ይገኛል፡፡
- በዚሁ መሠረት የተመሰከረላቸው 6 የቦቆሎ ምርጥ ዘሮች፣ የማሽላ ምርጥ ዘሮች፣ 6 የሰንዴ ምርጥ ዘሮች፣ 3 የጤፍ ምርጥ ዘሮች 3 የአኩሪ አተር ምርጥ ዘሮች ዉጤታማነታቸዉን ለማለየት በ238

የአርሶ አደር ማሣ ላይ የምርምር ሥራ ተካሂዳል፡፡ አርሶ አደሩም ከቴክኖሎጂው ጋር እንዲተዋወቅና ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

- የአፈርን መከላት ለመጠበቅ 5 የተለያዩ ዝርያዎችን በማፋላት በ38 የአርሶ አደር መሬት ላይ ምርምር ተከናውናል፡፡ ለ18 ሴት አርሶ አደር የጋሮ አትክልት ልማትና የምግብ አዘገጃጀት ስልጠና ተካሂዷል፡፡
- በአርሶ አደሩ አካባቢ በሚገኝ ተረፈ ምርት በነዐ አርሶ አደር ከብቶች ላይ የእንስሳት ማድለብ ቴክኖሎጂ ተከናውኗል፡፡
- ከአኩሪ አተር ሊሰሩ የሚችሉትን የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ዝግጅት ከነዐዐ በላይ ለሚሆኑ ሴት አርሶ አደር ስር 5 (አምስት) ሌሎች አርሶ አደሮችን በማደራጀት ቴክኖሎጂውን እንዲቀስሙ የተደረገ ሲሆን በአጠቃላይ ከነ453 በላይ አርሶ አደሮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ጋር እንዲተዋወቁ ተደርጓል፡፡

በዚሁ ኮሌጅ ከኮሪያ ፕሮጀክት ጋር በመሆን የተሰጡ አገልግሎቶች

- ምረታማነትን ለማሻሻል የKorean Project የተለያዩ የአትክልት ዝርያዎች በመስከና በ “Greenhouse” ደረጃ በማልማት (በመሞከር) ምርትና ምርታማነት የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ አምራቾች (ገበሬዎች) ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሠራ ሲሆን ፡
- ቴክኖሎጂውን ለማስፋፋት በጅማ ዞን ከሚገኙ ስድስት ወረዳዎች የልማት ሰራተኞችንና ሞዴል ገበሬዎችን በተለያዩ የአትክልት አመራረት ዘዴዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በኘሮጀክቱም አንድ መምህርት የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት እድል ተጠቃማ ሆናለች፡፡
- ፕሮጀክቱም በርካታየቀን ሠራተኞችና በለሙያዎችን ቀጥሮ በማሰራት ለአከባቢዉ ህብርተሰብ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡
- ፕሮጀክቱ በሰዉ ሀይል ልማት ላይ የሚሰራ ስለሆነ በሳለፍነዉ ግማሽ አመት ዉስጥ አንድ የኮሌጁ ሴት መምህር የሁለተኛ ዲግሪዋን ኢንዲትማር አድርገዋል፡፡
- ፕሮጀክቱ ቀጣይነት እንዲኖረዉ ህብረተሰቡና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላቶች ዕወቀቱንና ቴክኖሎጂዉን ኢንድቀስሙት እያደረገ ይጋኛል፡፡

IUC-JU የተሰኘዉ በዩንቨርሲቲዉ ዉስጥ ቆይታዉ የዕድሜ በለፀጋ ሊባል የሚችል ፕሮጀክትም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡን እየደገፈ ይጋኛል፡፡

- ፕሮጀክቱ ሀገራችን ያስቀመጠችዉን የዕደገትና ትራንስፎረሜሽን አጀንዳ ሊደግፍ የሚችል አለማ በመያዝ ከዩኒቨርስቲዉ ጋራ በጋራ ትብብር ለመስራት ተዋዉሎ በቆይተዉ ዉስጥ ይህ ነዉ የማይባል ሥራ ሰርተዋል፡፡
- ለትምህርትቤቶች የወንበርና የጠረጴዛ ድጋፌ አድረጓል፡፡
- ለትምህርትቤቶች የመፀደጃ ቤቶችን በመገንባት ለህብርተሰቡ አስረክቧል፡፡
- ፕሮጀክቱ በሰኮሩ አከባቢ አንድ የምርምር ማዕከል በመክፈት በወባና ሌሎች መሰል ጉደዮች ላይ ምርምር እያካሄደ በምርምሩ ዉጤትም የአከባቢዉ ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሆነኗል፡፡
- በሰኮሩ ካምፓስ የቬክተር ኮንትሮል የምርምር ዩንት ኢንሴክቴሪ ተቋቅሞ በግብዓቶች ተጠናክሮ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ገዳይ የወባ በሽታ ላይ የሚያደርገዉ ምርምር ተጠናክሮ እንድቀጥል ተደርጎ ለህብረተሰቡ በበሽታዉ ዙሪያ አጨጭር ስልጠና ለመስጠት ቅድሚያ ሁኔታዎች ተመቻችቷል፡፡

በነፃ የህግ አገልግሎት ለህብርተሰቡ የተሰጡ አገልግሎቶች

- በዚህ ግማሽ አመት ለ279 የአከባቢዉ ህብረተሰብ የህግ መማከር አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን በቁጥር 38 ለሚሆኑ የዩንቨርሲቲ ማህበርሰብም በህግ ዙሪያ ነፃ የመማከር አገልግሎት አግኝቷል፡፡
- **በ ሁለተኛ ሩብ አመት በጂማ ዞን ማረሚያ ቤት ዉስጥ ለሚገኙ □ህ□ □ታራሚዎችም** በህግና ከህግ ጋር ተያዥነት በላቸዉ ጉደይ ላይ ነፃ የመማከር አገልግሎት ተሰጠቷል፡፡
- **በ ሁለተኛ ሩብ አመት የህግ መማከር አገልግሎት ማዕከሉ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሺን ለማጠናከረየነት** 70578 **ብር በእርዳታ መልክ አግኝቷል፡፡**
- በጅማ ማህበረሰብ ሬድዮ ከህግ ማህደር በሚል ርእስ ለማህበረሰቡ በህግ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ትምህርቶች በሁለት ቋንቋዎች በየሳምንቱ በመደበኛ ፕሮግራም ተሰጥተዋል

በዩንቨርሲቲዉ ሆስፒታል ለህበረተሰቡ የተሰጡ አገልግሎቶች

- በሆስፒታሉ በኩል 12 ለሚሆኑ የልብ ህሙማን ህፃናቶች ነፃ የህክምና አገልግሎት እንድያገኙ ተደርጓል፡፡
- በ **ሁለተኛ ሩብ አመት** የዩንቨርስቲዉ ሆስፒታል የአይን ህክምና ማዕከል ከአዉስትራሊያ ሜዲካል ዩኒቨርስቲ አፍ ግራዝ ጋር በመተባበር በአይነቱ ልዩ በሆነዉ የ 'Retina' ቀዶ ጥገና አገልግሎት ለ11 ሰዎች በነፃ አገልግሎቱን ሰጥቷል

- በ **ሁለተኛ ሩብ አመት** ከአስትሪያ ከተጋበዙ የአይን ህክምና ባለሙያዎች ጋር በመሆን ለ 9 ሰዎች የአይን መንሸዋረር /Strabismus,የአይን ቆብ መዉረድና/Ptosis/ እና የመሳሰሉት የአይን ችግር ላለባቸዉ ሰዎች ከፍተኛ የቀዶ ጥገና አገልግሎት በነፃ ተሰጥቷል፡፡
- በአይን ህክምና 3764 ለሚሆኑ የጅማ ከተማና አካባቢዋ ተገልጋዮች የተኙቶ መተከምና በተመላላሽ የህክምና አገልግሎት አኝቷል፡፡
- 3750 ለሚሆኑ የአይን ህክምና ተከታታዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ውጤት5፡- በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተኮር ሬዲዮ በዩኒቨርሲቲው የተላለፉ ትምህርታዊ

ፕሮግራሞች የወሰዱት የዓየር ሰዓት 364

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በጅማ ማህበረሰብ ሬድዮ ከህግ ማህደር በሚል ርእስ ለማህበረሰቡ በህግ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ትምህርቶች ተሰጥቷል፡፡
- **በ□ህ ሚ□□ □□ኒቨርሲቲዉ የሥራ አፈፃፀምና ሌሎች ጉዳዮች ለዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብና ለአከባቢዉ ህብረተሰብ ይተላለፋል**፡፡
- **በተ□ ማሪም በማህበራዊ ጉደዮች፤ በጤና ነክ ጉደዮች፤ በህግና በሌለሎች ትምህር**ታዊ በሆኑ ጉደዮች □ሪ□ በ□□□ዬ **ለህብረተሰቡ □ተለላ□ል**፡፡ በአጠቃላይ ይህ የማህብረሰብ ሬዲዮ በሁሉም ማህብራዊ ጉደዮች ዙሪያ ሰፊዉን የአየር ሰዓት በመዉሰድ አስተማር በሆኑ ጉዳዮች ላይ በሁለት ቋንቋ (በአማረኛና በአፋን ኦሮሞ) የአከባቢዉ ህብረተሰብ መረደት በሚችል መልኩ ያስተላልፋል፡፡

3.1.4. □ሮ□ራም አራት /የትኩረት መስክ፡- -□ተቋማዊ ለውጥና መልካም አስተዳደር/የስራ አመራርና አስተዳደር

ስትራቴጂክ ዓለማ፡- ተቋማዊ ለውጡን በማጠናከር፡ ሳይንሳዊና ፍትሃዊ አገልግሎትን

በመስጠትና አስፈላጊዉን የገፅታ ግንባታ በመከናወን

የደንበኞችን/ባለድርሻ አካላትን እርካታ፡ አምነትና ጥቅም ማሳደግ

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 1፡- የተጠናቀቁና አገልግሎት መስጠት የጀመሩ (16) እና አዲስ

የተጀመሩ (4) **የካፒተል በጀት የግንባታ ፕሮጀክቶች ብዛት**

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በዚህ ግማሽ **ዓመት ከነባሮቹ ፕሮጀክቶች** የተወሰኑ **ተ□ናቀዬ** አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹም **ተገቢው ክትትልና አስተዳደራዊ ድጋፍ** እየተደረገላቸዉ ስለሆነ **በቀሪዎቹ የሥራ ግዜያት ተጠናቀዬ ሥራ ል□ስ□ምሩ የምያስችሉ□**እንዲሆኑ እየተደረገ ነዉ፡፡
- በግማሽ አመቱ በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ የአንደርግራዉንድ ኬብል ቀበራ በዉሉ መሠረት አሸናፍዉ ድርጅት ሳይቱን በመረከብ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ሌሎችም አዳድስ ፕሮጀክቶች በዕቅዱ መሠረት የዲዛይን ሥራ ተሰርቶላቸዉ ወደ ስራ እየተገባ ነው፡፡

የመደበኛ ዋናዋና ዉጤቶች

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 1፡ የተከናወኑ የተቋም ማሻሻ□ ስራ- ች ብዛት (13)

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- ዩኒቨርሲቲዉ ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፋ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት በነበረዉ መዋቅር ዉጤታማ የሆነ ሥራ መስራት እንዳልተቻለ ስለተደረሰበት አንድአንድ ደግም ልታዩ የሚገባቸዉ የዩኒቨርሲቲ ክፍሎች በማየት የመዋቅር ማሻሻያ የሚያስፈልገቸዉ ክፍሎችን ለይተዉ በመወቅ ወደ ማሻሻያ ስራ ተገብቶ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ከለዉ የስራ ስፋት በማየት ሁለት ምክትል ፕሬዚደንቶች(የምርምርና ህብረተሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት እና የቢዚነስና ልማት ምክትል ፕሬዚደንት ሲሆኑ በአጠቃላይ አራት ምክትል ፕሬዚደንቶች እነሱም፡- የአካደሚክ ምክትል ፕሬዚደንት፤ የአስተዳደርና ተማሪዎች ጉደይ ምክትል ፕሬዚደንት፤ የቢዚነስና ልማት ምክትል ፕሬዚደንትና የምርምርና ህብረተሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት) ናቸዉ፡፡ በተጨማሪ ኢንዲኖሩ ተደርጎ ከብዙ ግዜ ጥናት ቦኃላ በሴኔቱ ከፀደቀ ቦኃላ በቦርዱ እንዲፀድቅ ተደርጎ ፀድቋል፡፡ በተጨማሪም ኮሌጆች አሁን ያሉበት የሥራ ሁኔታ ታይቶ በአንድ የኮሌጅ ዲን ሁሉም ሥራዎች ለማከናወን ከፍተኛ የሆነ ጫና እያሰደረ ስለሆን በኮሌጆቹ ስር በሚገኙት የትምህርት ክፍል ብዛት ተይቶ (አምስትና ከዚያ በላይ ከሆነ) ለኮሌጁ አንድ የአካደሚክ ምክትል ዲን እንዲመደብላቸዉ ተጠንቶ በዚሁ መሠረት ወደ ስራ ለማግባት ሂደት ላይ ይጋኛል፡፡ ሌሎች የስራ ክፍሎችም በዚሁ መልኩ የተጠኑ ሲሆን ጥናቱ እንደአለቀ ወደ ትግባራ ለመግባት ዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡
- የተዘገጃዉ ሚዛናዊ ዉጤት ተኮር ዕቅድ በዘርፉ ላሉ የዩኒቨርሲቲ አካላት እንዲወርድ ተዳርገዋል፡፡
- በዚሁ መሠረት ሁሉም የአካዳሚክም ሆነ የአስተዳደር ሠራተኞች የየግል ዕቅደቸዉን አዘጋጅተዉ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡
- አፈፃፀሙ በአዉቶሜሽን የተደገፈ ለማድረግ **የዩኒቨርስቲያችን የአይሲቲ ባለሙያዎች** BSC **ሶፍትዌሩን በተሳካ ሁኔታ□ ሠርተዉ □ ርሰ□ል**፡፡
- በሶፍትዌሩ አጠቃቀም ላይ ለዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ ስልጣና ለመስጠት በወጠዉ ፕሮግረም መሠረት **በቅድሚያ ለሴኔት አባላት አግባብ ያለዉ ስልጠና ተሰጥቷል**
- በመቀጠልም የሁሉም ዘርፍ ኃላፊዎች የዩኒቨርስቲው ኘሬዚደንት ጭምር በተገኙበት ለሁሉም የት/ት ክፍል ኃላፊዎች ሁለት ዙር ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

- **በቀ□□** በየኮሌጁች ያሉ የኢይሲቲ አስተባባሪዎች በየኮሌጃቸው ላሉ ለሁሉም ሠራተኞች ስልጠናውን በባለቤትነት እንዲሰጡ ለማድረግ እንዲችሉ ዝርዝር ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን በቅርቡ ሥራቸውን ያጠቃልላሉ፡፡
- □ተከታታይ ማሻሻያ ስርዓትን (keizen) አጠናክሮ ማስቀጠል ስራ የተሰራ ነው ፡
- **የትምህርት ልማት ሠራዊት ግንባ**ታ የትምህርት ሚኒስቴር በሰተላለፈዉ መመሪያ በመተጋዝ የለዉጡ ፅንሰ ሀሰብ በዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ ዉስጥ ሰርፆ እንደገባ ለማድረግና ወደ ተጨባጭ ትግባራ ለማግባት ዩኒቨርሲቲዉ የበላይ አመራርን ጨምሮ ሌሎች የቢሮ ኃላፍዎች የተገኙበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የነ፤5 ፅንሰ ሀሰብ ግንዘቤ ከተወሰደ ቦኃላ በነ፤5 በማደረጀት ወደ ተጨባጭ ትግበራ ተገብቷል፡፡ አደረጃጀቱም አልቆ ሁሉም ቡዲኖች የየራሳቸዉን ዕቅድ በማዘገጀት ለአፈፃፀሙ ስተራቴጅ አዘገጅቷል፡፡
- ***መምህራን በየሚያስተምሩት የት/ት አይነት*** (course team) □ከኬዝ ቲም ***እንዲደራጁ የተደረገ*** ሲሆን በየት/ት ክፍላቸው ደግም በልማት ቡድን ተደራጅተዋል፡፡
- **በአጠቃላይ 178** የልማት ቡድኖች በአካደሚክ ዘርፍ **ተ□ራፀ ተ□ል**፡፡
- **የኮንትራትና ጊዜያዊ ሰራተኞችን በቋሚ መደቦች ላይ የመመደብ ስራ በተቀደለት መሠረት** እየተከነወነ ይገኛል፡፡ ይህም ማለት በዚህ ግማሽ አመት 85 በመቶ ያህሉ ተጠናቆ ሠራተኞቹ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡
- **የጅማ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የማዋቀር ሥራ ደረጃ በደረጃ** እየተከሄደ ያለ ስሆን በዚሁ መልኩ ደግሞ ኢንስቲትዩቱን ወደ ክቶ ፉረዲሳ ለማዛዋር እየተደረገ ያለዉ ሥራና ቅዲሚያ ሁኔታዎችን የመማቻቸት ሥራ በተጠናከረ መልኩ እየቀጠለ ነዉ፡፡
- የየኬዝ ቲሙም ሆነ የልማት ቡድኖችን ተግባርና ኃላፊነት የያዘው ሙሉ ዶኩመንት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- የአስተዳደር ሠራተኞችም በየሥራ ባኅሪያቸው ተፈጥሮአዊ የሥራ ሂደት ፍሰት መሠረት በነ፡5 የተደራጁ ሲሆን የየግልና የልማት ቡድኑን ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡
- በአጠቃላይ 748 የነ፡5 ቡድኖች በአስተዳደር ዘርፍ ሲመሠረት ሁሉም ቡድኖች የየራሰቸዉን ሱፐርቫይዘር አቋቅመዋል፡፡
- ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከበላይ አመራር አካል ጀምሮ እስከ እያንዳንዱ ኮሌጅ ድረስ ያለውን የትምህርት ልማት ሠራዊት ክንውንና ዝርዝር አፈጻጸሙን የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ የሱፐርቪዥን ቡድን በየደረጃው ለማቋቋም ኘሮግራም ወጥቶ እየሄድንበት ነው፡፡ በዩኒቨርስቲው ኘሬዚደንት የሚመራ 7 አባላት የሚገኙበት ዩኒቨርስቲ አቀፍ የሱፐርቪዥን ቡድን ተቋቁሟል፡፡
- በኮሌጅ ደረጃ እንዲሁም በት/ት ክፍል ደረጃ 3/3 አባላት የሚገኙበት የሱፐርቪዥን ቡድን ተቋቁሞ አፈጻጸሙን በቅርብ እየተከታተለው ነው፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት-2፡- በተቀናጀ የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ስርዓት (MIS) **ና**

አይሲቲ ዙሪያ የተከናወኑ ፕሮጀክቶች ብዛት (19)

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- **ለነባር የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት** (MIS) **ሙሉበሙሉ ወደ ትግበራ ለማግባት አስፋላግ የሆኑ ዕቃዎች** (devises) ለመግዛት ጫረታ ወጥቶ በጫረታዉ ላይ ግምገማ እየተከሄደ ይጋኛል፡፡
- **ለአዲስ 11 ፕሮጀክቶች የዲዛይን፡ የግዢና አቶሜሽን ስራ ተካሂ□□ል፡፡**

በአመቱ መጨረሽ የሚጠበቅ ዉጤት3፡- የተከናወኑ የስነምግባር፡ ፀረሙስናና የቅሬታ ማስተናገጃ እንቅስቃሴዎች ብዛት (3)

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- በሳለፍነዉ ግማሽ አመት የዩንቨርሲቲዉ የስነምግባርና ፀረ ሙስና ቢሮ በተማሪዎች መካከል የፀረ-ሙስና ክለብ ኢንዲቋቋም አድርጎ ክለቡም ተቋቅሞ ከቢሮዉ ጋር በመነበብ ስራ እየተሰራ ይጋኛል፡፡ በመጀመረያዉ ሩብ አመት 40 ሠራተኞች ሀብታቸዉን አስመዝግቦ ከዚህ ዉስጥ ሦስቱ የምስክር ወረቀት መረከባቸዉን ሪፖርት ተደርጎ ነበረ፡፡ አሁንም በዚህ በሁለተኛዉ ሩብ አመት 20 የትምህርት ክፍል ኃላፍዎች ከፌዲራል የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተለካዉ የሀብት ማስመዝገቢያ ቅፅ ላይ ሀብታቸዉን በማስመዝገብ የምስክር ወረቀት ተረክቧል፡፡

በክራይ ሰባሳብነትና ብልሹ አሰራሮች ላይ ተወሰዱ እርምጃዎች፡-

ዩንቨርሲቲዉ ለክራይ ሰብሰባነት የተጋለጡ የስራ ሂደቶችን በመለየት ግለሰቦቹ ለዚህ ብልሹ አሠራር ተጋላጭ እንዳይሆኑ፡-

- የቡድንና የግለሰብ ፈፃሚዎችን አቅም ለመገንባትና በብልሹ አሰራሮች ላይ የተለያዩ ስልጠናዎች ለአተዳደር ሰራተኞች ተሰጥቷል፡፡
- በየደረጃዉና በየዘርፉ ኮሌጆች፤የትምህርት ክፍሎችና ሌሎች የስራ ክፍሎች በየጊዜዉ የዉይይት መድረኮችን በማዘጋጀት በአጠቃላይ የስራ ሂደት ላይ በመወያየት ላጋጠሙ ችሮች የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፡፡
- የስራ ክፍሎች ለብልሹ አሰራርና ክራይ ሰብሳብነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ በየግዜዉ በዉስጥ አዲታችን የየወሩ የአዲት ሂሳብ አዲት ይደረጋል፡፡ የፕሮጀክት ሂሳብ አዲትም ተሰርቶ ሪፖርቱ ለሚመለከተዉ የበላይ ሀላፊ እንዲቀርብ ተደርጓል
- የ፤5 አደረጃጀትም በብልሹ አሰራሮች ላይ ከፍተኛ ጫና እያሰደረ ይገኛል፡፡
- የካይዘን መሰረተ ሃሳቡንና አተገባበሩን አስመልክቶ ከሁሉም ኮሌጆች፤ከተማሪዎች አገልግሎትና ከንብረት ክፍል ለተዉጣጡ ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል

- በዩንቨርስቲዉ የሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮችን ለማስተካከልና ሙስናን ለመከላከል ዩኒቨረስቲዉ የፀረ ሙስና ቢሮ ከፌደራል የፀረ ሙስና ቢሮ ጋር በመተባበር በተለያየ ጊዜ በየዘርፉ ግምገማ እንዲደረግ አድረጓል፡፡በተጨማሪም የስነ ምግባር መኮንን ባልነበረባቸዉ ኮሌጆች ባለሙያዎች እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ከየክፍሎቹና ከግለሰቦች የሚመጡ ወደ 20 የቅሬታና ሙስናን የማጋለጥ ጥቆማዎች በመዉሰድ ለ15ቱ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊዉን መፍትሄና እርምጃዎች ወስዷል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ግማሽ አመት 24 ቅሬታዎች ቀርቦ 19ኙ (አስራ ዘጠኙ) ህገዊ የመፍትሄ እርምጃ ተወስዷል፡፡
- ከ20 በላይ የሚሆኑ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ከፌደራል የፀረ ሙስና ቢሮ በተላከዉ የሃብት ማስመዝገቢያ ቅፅ በማስሞላት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወስዷል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 4፡- የዉጭ ግንኙነት በማጠናከርና በገፅታ ግንባታ ላይ የተሰሩ ስረዋች ብዛት 18 ይሆናሉ፡፡

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- ዩንቨርሲቲዉ በሳለፈነዉ ግማሽ አመት ዕቅድ አፈፃፀም ዉስጥ ከተለያዩ ሀገር ዉስጥና ዉጭ ከሚገኙ ተቋማት ጋር አካደሚያዊ የጋራ ትብብር ለመፍጠር አቅዶ ከአስራ ሁለት (12) ዉጭ ሀገር ተቋማት ጋር በተላያዩ የመማር መስተማር እንዲሁም የምርምር ሥራዎች ዙሪያ አብሮ ለማስረት የጋራ ስምምነት ተፈጥሯል፡፡
- ነባር ግንኙነቶችን ለማጠናከርና አብሮ መስራት ቀጣይነት እንዲኖረዉ ለማድረግ ከዚህ በፊት የተፈራረምነዉን ዶክመንቶች አሰባስቦ የመመዝገብና የመደረጀት ስራ ለመስራት ታቅዶ በግማሽ አመቱ ተከናዉኗል፡፡
- በተለያዬ መልኩ ዩንቨርሲቲያችን የማስተወወቅ ስራ ለመስራት ታቅዶ ዩንቨርሲቲዉን ሊያስተወዉቅ ይችላል በተበሉ መንገዶች በመጠቀም በሀገር ዉስጥና ዉጪ የማስተዋወቅ ሥረዉ እየተሰራ ይጋኛል፡፡
- በዩንቨርሲቲዉ የዉጭ ግንኙነት ቢሮ በኩል የአሉሚኒ ኮንፈረንስ ለማካሄድ አስፈላግዉ ቅዲሚያ ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ ይጋኛል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ውጤት5፡- የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊ ግብዓቶችን ለማሟላት በፋይናንስ፡ በግዢ፡ በፕላኒንግ፡ የተሸከርካሪ ስምሪትና ጥገና፡ የሰው ሃብት አመራርና አዲት አገልግሎት የተሰጡ ድጋፎች ብዛት

በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- ዩንቨርሲቲዉ ለቀጣይ አመት የሥራ ዘመን ቀደም ብሎ ሥራዉን የማቀድና ዕቅዱንም ለሚመለከተዉ አካል
- የማሰወቅ ሥራዉ ከዕለት ዕለት የማይለየዉ የሁልግዜ ተግባሩ ነዉ፡፡ በዚሁ መሠረት በ2006 ዓ.ም. የሚሰሩ ሥራዎችን አስቀድሞ በማቀድ የዩንቨርሲቲዉ የስራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎት የማሰባሰብ ሥራና ሌሎች ግብዓቶችም በዚሁ መልኩ የማሰባሰብ ሥራዎች ወቅቱን ጠብቆ ተሰርቷል፡፡ በተለይ ለመማር መስተማር ሥራ

የሚዉሉ ግብዓቶችን በወቅቱ ለማስገባትና ሂደቱ ሰለማዊ ኢንዲሆን ሁሉም ግብዓቶች በተሰካ ሁኔታ ተፈፅሚል፡፡

- ተማሪዎቻችን ወይም ደንበኞቻችን ለተግባር ልምምድ እነዲሁም መምህራን ለምርምርና ህብረተሰብ አገልግሎት ወደ ህብረተሰቡ ስወጡ በትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ዕጥረት እንዳይፈጠር በቅዲሚያ ታቅዶ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ ያለምንም እንግሊት የመማር መስተምርም ሆነ የተግባር ልምምዱ በተሰካ ሁኔታ ተከናዉኗል፡፡
- በሰዉ ሀይል ፍላጎት ላይም በቅዲሚያ ፍላጎት በማሰበሰብና እንዲሁም ግዜያዊና ኮንትራት ሠራታኞችን ወደ ቋሚ መደብ የማምጣቱ ሥራ አስቀድሞ በማቀድ የመምህራን፤ የበላሙያና ሌሎች የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር በወቅቱና በተሰካ መልኩ ተካሂዷል፡፡ ጊዚያዊና የኮንትራት ሠራተኞች ወደ ቋሚ መደብ የማምጣቱ ሥራ በተሰካ መልኩ ተፈፅሚል፡፡
- ዩንቨርሲቲዉ በርካታ ነባር የቢሮዎች፤ የመመሪያ፤ የተማሪዎች መደሪያ፤ የተማሪዎች መመገቢያ፤ የቤተመጽሐፍቶች እና ሌሎች ሕንፃዎች ያሉት ሲሆን እነኝህ ህንፃዎች ደግሞ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ በመሆናቸዉ ከግዜ ወደ ግዜ እየተበላሹ እንዳይሄዱና በግዜ ጥገና ማድረጉ ወሳኝ ስለሆነ ተማሪዎች ወደ ቅጥረ ግቢ ከማግባታቸዉ በፍትና እንዲሁም ከገቡ ቦኃላ ክትትል እየተደረገ ሙሉ በሙሉ ጥገና ተደርጎላቸዋል፡፡ በጥቅሉ 150 ለሚሆኑ መሣርያዎች፤ ተሽከርካሪዎችና ህንፃዎች ተገቢዉ ጥገና ተደርጎላቸዋል፡፡

በአመቱ መጨረሻ የሚጠበቅ ዉጤት 6፡- የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶችን በማጠናከር ከጠቅላላ መ□በኛ

በጀት ያለውን ድርሻ 3.0 በመቶ መድረስ

ተ.ቁ	የኢንተርፕራይዙ ሥም	የዓመቱ ዕቅድ	የ2ኛ ሩብ ዓመት የተጣራ ገቢ			እስከ 2ኛሩብ አመት			ምርመራ
			ዕቅድ	ክንውን	ክንውን በመቶኛ	ዕቅድ	ክንውን	ክንውን በመቶኛ	
1	የፋርማሲቲካልስ አስመጪና አከፋፋይ		-	-	-	-	-	-	በ4ኛ ሩብ ዓመት
2	የፋርማሲቲካልስ ችርቻሮ ንግድ								
	2.1. ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር 1	2,697,094	674273	764058	113	1,348,546	1,177,895	87	
	2.2. ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር 2	423,108	105,777	23,122	21	211,554	62,131	29.3	
3	ኪቶ ፋርዲሳ ግ/ልማት ኢንተርፕራይዝ	4,209,904	802,476	545,421	68	1,604,952	545,421	34	
4	ቁሳቁስ ማምረቻና ጥገና ኢንተርፕራይዝ	3,832,476	958,119	2,544,686	265	1,416,238	2,544,686	179	
5	ንግድ ኢንተርፕራይዝ	699,353	174,838	77,500	44	349,676	155,000	44	
6	ክበባትና መዝናኛ አገልግሎት በዋናውና በሆስፒታል	623,476	155,869	171,667	110	311,738	327,536	105	
7	የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ	2,010,000	502,500	532,249	100.6	1,005,000	1,034,749		
	Total		3,373,852	**4,658,703**	**138**	**6,247,704**	**5,847,418**	**93**	

ግማሽ አመቱ የተከናወኑ ዝርዝር ታግባራት፡-

- **የመድሃኒትና ሜዲካል ሰፕላይስ ጅምላ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት አስፈላጊው □ርማሊቲና የንግድ ፍቀድ ማዉጣት ሥራ ተከናዉነዋል፡፡**
- **የተጀመረውን የቁሳቁስ ማምረቻ ፕላንት ግንባታ የማጠናቀቅ ስራ በተጠነከረ ሁኔታ እየተከነወነ ይጋኛል፡፡**
- **በ7ቱም ገቢ ማመንጫ ኢንተርኘራይዞች የፋይናንስና የንብረት ደረሰኞችና ሰነዶችን ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ለማዋል በተደረገዉ እንቅስቀሴ በሁሉም ኢነተርፕራይዞች ተሰክቶ ከክበባትና መዝናኛ አገልግሎት ብቻ ይቀራል፡፡**
- **ለ7ቱም ገቢ ማመንጫ ኢንተርኘራይዞች መተዳደሪያ ደንብ ከአንዱ በስተቀር ለሁሉም ተዘጋጀቶ ሥራ ላይ ለማዋል እስክፀድቅ ድረስ እየተጠባበቅን ነዉ፡፡**

ክፍል ሁለት

3.2.1. የተቋማዊ ለውጥ ትግበራ አፈፃፀም ሪፖርት

ጅማ ዩኒቨርስቲ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት □በልዓ ዉ□ታማ ለማ□ረግና ራዕዩን ከግብ ለማድረስ በተለወጠ አደረጃጀትና አሠራር አበክሮ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ሀገራዊውን የልማትና የዕድገት መርሀ-ግብር ለማሳለጥ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ ዩኒቨርስቲው ብቃት ያላቸውን ምሁራን በማፍራት የራሱን ድርሻ ለመወጣት ተጨባጭ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ መላው የዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብ ወደ ለውጥ መንፈስ እንዲገባና የተቋማዊ ለውጥ ሂደቱ ይበልጥ መሠረት □እ□□□ እንዲሄድ ለማድረግ አበክሮ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ የተቋማዊ ለውጡ የትኩረት አቅጣጫና ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

3.2.1.1. የትምህርት ልማት ሠራዊት ግንባታ

1. መንግስት ያስቀመጠዉን ልማታዊ አቅጣጨን ተከትሎ የእድገትና ትራንስፎረሜሽን አጀንዳ ዕዉን ለማድረግ ዩኒቨርሲቲዎች የተሰጣቸዉን ኃለፍነት እየተወጡ እንደሆነ ግልፅ ነዉ፡፡ በዚሁ መሠረት ዩኒቨርሲቲያችን ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን መሰካት ተጨባጭ መሰሪያ የሆኑትን መንግስት ያስቀመጣቸዉን ስትራቴጅዎች በመጠቀም የመማር መስተማር፤ የምርምር እና የህብረተሰብ አገልግሎትን የተሰካ እንዲሆን የትምህርት ልማት ሠራዊት ግንባታ ማደረጀት አንዱና ዋንኛ መሣሪያ በመሆኑ የትምህርት ሚኒስቴር በሰጠዉ መመረያ መሠረት የ1ለ5 አደረጃጀት ፅንሰ ሐሰብ በዩንቨርሲቲዉ ማህብረሰብ መካከል ሰርፆ እንዲገባ ማድረግና ማደረጃቱ ወሳኝ የዚህ ግማሽ አመት ስራ ነበረ፡፡ባለፈው ዓመት ከተደረገው ጥረት ባሻገር በቅርቡ ከትምህርት ሚኒስቴር በተላከልን የትምህርት ልማት ሠራዊት አደረጃጀት ማንዋል መሠረት ሁሉንም የትምህርት ክፍሎች ኃላፊዎችና ዲኖችን ፤ ዳይሬክተሮች እንዲሁም የተማሪዎች መማክርት አባላት የተገኙበት፣ በተመሳሳይ መልኩ ሁሉንም የሥራ ኃላፊዎች ያሳተፈ ሁለት ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ከተሰጠ በኋላ ወደ ትግበራ ተገብተዋል፡፡በጥቅሉ የትምህርት ልማት ሠራዊት ግንባታ በሚከተለዉ መልኩ ተከናዉኗል፡፡

   1.1. በመጀመረያ የዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ ስለ 1 ለ 5 አደረጃጀት ግንዘቤ እንድኖራቸዉ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መስራቱ አማራጭ የሌለዉ መንገድ ስለነበረ ሁሉም የዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ ደረጃ በደረጃ የ1፡5 ፅንሰ ሀሰብ እንድቀስሙ ተደርገዋል፡፡ ፅንሰ-ሀሳቡም በሁሉም የዩንቫርሲቲ ማህብረሰብ መካከል ታግባራዊ እንድሆንና ማህብረሰቡም አምኖ እንድቀበል ማድረግ ዋንኛ ሥራ ስለነበረ በዛዉ መልኩ ማህብረሰቡን ከማሳመን በሻገር አመስራረቱም ስር የሰደደ እንዲሆን የማያወዘግብ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በሁሉም ሴክተሮች በተማሪዎች መካከል፤ በመምህራን እና በአስተዳደር ሠራተኞች መካከል ስር የሰደደ ለወጣዊ ቡድን አደረጃጀት እንድኖር ተደርግዋል፡፡

   1.2. ከዚህ በመቀጠልም ወደ አደረጃጀት ተገብቶ አደረጃጀቱም በሚከተለዉ መልኩ ተፈፅሟል፡-

- መምህንን በሚያስተምሩት የት/ት አይነት (course team) በኬዝ ቲም እንዲደራጁ የተደረገ ሲሆን በየት/ት ክፍላቸው ደግም በልማት ቡድን ተደራጅቷል፡፡ በአጠቃላይ 178 የልማት ቡድኖች በአካደሚክ ዘርፍ ተደራጅቷል፡፡
- የየኬዝ ቲሙም ሆነ የልማት ቡድኖችን ተግባርና ኃላፊነት የያዘው ሙሉ ዶኩመንት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- የአስተዳደር ሠራተኞችም በየሥራ ባኅሪያቸው ተፈጥሮአዊ የሥራ ሂደት ፍሰት መሠረት በ1፡5 የተደራጁ ሲሆን የየግልና የልማት ቡድኑን ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡ የዕቅድ ዝግጅቱም በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ተጠናቆ ወደ ሙሉ ትግባራ እንደሚገባ ይተመናል፡፡
- በአጠቃላይ 748 የ1፡5 ቡድኖች በአስተዳደር ዘርፍ ሲመሠረት ሁሉም ቡድኖች የየራሰቸዉን ሱፐርቫይዘር አቋቅሟል፡፡
- ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከበላይ አመራር አካል ጀምሮ እስከ እያንዳንዱ ኮሌጅ ድረስ ያለውን የትምህርት ልማት ሠራዊት ክንውንና ዝርዝር አፈጻጸሙን የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ የሱፐርቪዥን ቡድን በየደረጃው ለማቋቋም ፕሮግራም ወጥቶ እየሄድንበት ነው፡፡ በዩኒቨርስቲው ፕሬዚደንት የሚመራ 7 አባላት የሚገኙበት ዩኒቨርስቲ አቀፍ የሱፐርቪዥን ቡድን ተቋቁሟል፡፡
- በኮሌጅ ደረጃ እንዲሁም በት/ት ክፍል ደረጃ 3/3 አባላት የሚገኙበት የሱፐርቪዥን ቡድን ተቋቁሞ አፈጻጸሙን በቅርብ እየተከታተለው ነው፡፡
- በዚሁ መሠረት በየሳምንቱ ዓርብ ሁሉም ኮሌጆችና ዘርፎች አንላይን ሪፖርት ለፕሬዚደንቱ ይልካሉ፡፡
- **በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎችም በየሴክሽናቸው በ1፡5 የተደራጁ ሲሆን** ግንባር ቀደም ተማሪዎች ተለይተው **☐እርስ በርስ ☐መማማሩንና የመደጋገፉን ጥረት ጀምረዋል**፡፡ አማካሪ መምኅራንም ተመድበውላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ 3300 ቡድኖች በተማሪዎች ዘርፍ ተቋቁሟል፡፡
- በተማሪዎች (peer learning) አደረጃጀትና አፈፃፀም ላይ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲዉ በላድርሻ አካለቶች ጋር ዉይይት ተደርጎ (peer learning) አድስ ፅንሰ-ሀሰብ ቢሆንም ይህ ፅንሰ-ሀሰብ በሳይንስ ደረጃ የሚደገፍና የሚበረታታ ሀሰብ እንደነበረ በመግለፅ አሁንም ቢሆን ለአፈፃፀሙ የሚያስቸግር እንደማይሆን በዉይይቱ ላይ የጋራ አቋም ተወስዶ ተፈፅሟል፡፡
- የተማሪዎችን (peer learning) ፍሬአማ ለማድረግ በኮሌጆች ደረጃ ዝርዝር የድርጊት መርሀ-ግብር አውጥተው በየሳምንቱ ለተማሪዎች የሚደረገውን የማብቃት ሥራ ጀምረዋል፡፡
- በተመሳሳይ ሁኔታ የተማሪዎች ማኅበራዊ ድረ ገጽ ተከፍቶ የትምህርት ልማት ሠራዊት ጠቀሜታ ላይ ተያያዥነት ያላቸው ሀሳቦች እየተንሸራሸሩበት ተደርገዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲዉ የልማት ሠራዊት ግንባታ በቡድን የአደረጃጀት መረጃ

ቁጥር	የተደራጁ ቡድኖች ብዛት			ምርመራ
	የአስተዳደር ሠራተኞች	የአካ□ሚ□ ሠራተኞች	ተማሪዎች	
1	748	178	3300	

3.2.1.2. በመልካም አስተዳደር □□ኒቨርሲቲዉ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

- የዩንቨርስቲው የበላይ አመራር ዩኒቨርስቲው ተልዕኮውን በሚገባ ሊወጣ የሚችለው የለውጥ ፕሮግራሙን ቁልፍ ሥራ አድርጎ በማከናወንና አሳታፊ በሆነ አመራር መሆኑን ተገንዝቦ መላውን የዩኒቨርስቲውን ማኅበረሰብ ለዚሁ ግብ በማሰለፍ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት በተለያየ እርከን በሚኖሩ ስብሰባዎች በቂ ግንዛቤ ከመፍ□ር ባሻ□ር፣ በየዘርፉ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በመስጠትና በመገምገም አፈጻጸሙን በቅርብ ይከታተላል::
- የቡድንና የግለሰብ ፈጻሚዎችን አቅም ለማጎልበት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸው □እንዲጎለብትና አፈጻጸማቸው ውጤታማ □እንዲሆን በማድረግ ላይ ነው::
- ከዚህም በተጨማሪ ሠራተኞችም በየመድረካቸው (በየኮሌጆች፣ ት/ት ክፍሎችና በየሥራ ዘርፋቸው) ተመሳሳይ የውይይት መ□ረኮች □እያዘጋጁ በለውጥ አፈጻጸም ዙሪያ ምክክርና ውይይት ያደር□ሉ::
- በየመድረኮቹ የሚነሱ አስተያየቶችን በመለየት ተገቢው የእርምት □እርምጃ □እንዲወሰድ ለየሚመለከታቸው ይላካሉ::
- በአጠቃላይ መላው የዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብ በለውጥ አስፈላጊነት ላይ በቂ ግንዛቤ □ዓ ሮ □እንዲጎቀሳቀስ ያላሰለሰ ጥረት ተደርጓል:: በመደረግም ላይ ነው::
- በ2005 ዓ.ም. የታዩትን የአፈጻጸም ክፍተቶች ነቅሶ በማውጣት በዚህኛው ዓመት ተገቢ እርምት እንዲወሰድባቸው በዝርዝር ቀርበዋል::
- በኃይማኖት አክራሪነትና በሚያስከትለው አደጋ ላይ፣ እንዲሁም ተቻችሎ በመኖር ላይ የጠራ ግንዛቤ ተይዟል::
- ተመሳሳይ ስልጠና ለመላው የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ተሰጥቷል::
- ተማሪዎቹ በብሔር ፣በጎሳ □እንዲሁም በሃይማኖት ልዩነት □እንዳይፈጥሩና በማቀራረብ የወዳጅነት ስሜት እንድኖራቸዉ ሀገራዊ የብሔር ብሔረሰብ ቀን በዩንቨርቲ ደረጃም

ኢንዲከበር ተደርጎ በባዓሉ ላይም የዩንቨርሲቲዉ የበላይ አመራር ፕሬዚዳንቱን ጨምሮ በአብሮነት ላይ ዩኒቨርሲቲዉ ያለዉን አቋም በመግለፅ ተማሪዎቹም ይህንን ሀሰብ በመዉሰድ ወደ ታግባር ኢንዲቀይሩት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርተዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥና ዉጭ በደህንነት ዙሪያ የተሰሩ ስራዎች

በዩኒቨርሲቲዉ የመማር መስተማር የሥራ ሂደት በሰለማዊ መንገድ እንድከናወን በደህንነት ላይ የተሰሩ ሥራዎች፡-

1. የተማሪዎችን ደህንነት ለማስጠበቅ የተሰሩ ስራዎች
   1.1. እንደሚተወቀዉ ዩንቨርሲቲያችን በቅርብ ርቀት ላይ ሦስት ከምፓሶች ከዋናዉ ግቢ ዉጭ የሚገኙ ሲሆን እነሱም የግብረናና እንስሰት ህክምና ኮሌጅ፤ የቴክኖሎጅ ኢነስቲትዩትዚህ ዉስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ከዋናዉ ግቢ በተወሰኑ ክሎ ሜትር ርቆ የሚገኙ ሲሆን የቢዚነስና ኢኮኖምክስ ኮሌጅ ግን ከዋናዉ የግቢ አጥር በስተደቡብ 12 ሜትር ብቻ ርቆ ይጋኛል፡፡ ይህ ካምፓስ ካለዉ የቦታ ጥበትና እንዲሁም የተማሪዎች መመገቢያ ካፍቴርያና ቤተመጽሐፍት በዋናዉ ግቢ ስለምገኝ ተማሪዎች በየግዜዉ ወደ ዋናዉ ግቢ ይመላለሳሉ፡፡ ሆኖም ግን በዋናዉ ግቢና ከምፓሱ መካከል ሀገር አቀፍ የመከና መንገድ አቋርጦ ስለሚያልፍ በየግዜዉ የትራፍክ መጨናነቅ ከመታያቱም በላይ ተማሪዎቹ ከካምፓሱ ወደ ዋና ግቢ ለምግብም ሆነ ለሌላ ጉደይ ስመላለሱ የመከና አደገና የፆታዊ ትንኮሳ ልደርስባቸዉ ስለሚችል ዩኒቨርሲቲዉ ይህንን ጉደይ ግንዘቤ ዉስጥ በመስገበት የተማሪዎቹን ደህንናት ከመጠበቅ በተጨማረ ሥራን ለማቀለጠፍ በአየረ ላይ ተሻጋር ድልድይ (Suspension bridge) ከዋና ግቢ ወደ ቢዚነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የሚዋስድ ተገንብቶ በቅርብ ግዜ ዉስጥ ስራ ይጀምራል፡፡
   1.2. ዩኒቨርሲቲያችን ተማሪዎቹንም ሆነ የግቢዉን ማህበረሰብና ንብረት ከአደጋ ለመከለካል ከጂማ ከተማ መስተደደርና ህብረተሰብ እንዲሁም ከጂማ ዞን መስተዳደርና ህብረተሰብ ጋር ተቀናጅቶ ማስራት የለቀ ደህንነት ኢንደሚኖር በመገንዘብ አንድ የጂማ ዩኒቨርሲቲ ኮማንድ ፖስት 25 አበላት ያለዉና በዩንቨርሲቲዉ የሚመራ ኮሚቴ ተመስርቶ በአሁኑ ሰዓት በድህንናት ዙሪያ በየግዜ እየተገነኙ ዉይይት ያደርጋሉ እንዲሁም ያገጠሙ ችግሮችም ካሉ በወቅቱ መፍትሄ ያፈላልጋሉ፡፡
   1.3. የዩንቨርሲቲዉ ጥበቃና ደህንናት ቢሮ በተማሪዎች መካከል ምንም አይነት ወከባና አለመረገጋት እንዳይኖር ለማድረግ በተማሪዎች መከከል ከተማሪዎቹ የተወጣጡ የሰላም አስከባር ኮሚቴ ተደረጅቶ ስራ እየተሰራ ይጋኛል፡፡ ቢሮዉ ከሁሉም የተማሪዎች ክባባት ጋር በቅንጂት እየሰራ ይጋኛል፡፡
   1.4. ዩኒቨርሲቲዉ ከያዛቸዉ አላማ (የመማር መስተማር፤ የጥናትና ምርምር እና ማህብረሰብ አገልግሎት) ዉጪ ሌሎች የተማሪን ቀልብ እና አቋሚ የሚያዉኩ ጉደዮች ለምሳሌ ሃይማኖታዊ አለባበሶችን፤ አመጋገቦችን፤ ሃይማኖታዊ ጥቅሶችን፤ መዝሙሮችን፤ ፀሎትን ወይም ስግደትን ፤ ሃይማኖታዊ ሰበካዎችን፤ ጉባኤዎችን እና የመሰሰሉት የዩኒቨርሲቲዉን አለማ ሊያስቱ የሚያስችሉ ድርግቶችን በዩኒቨርሲቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ እንደይከናወንና ተማሪዎች ለትምህርታቸዉ ብቻ ትኩረት እንድሰጡ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጀ ለዩኒቨርሲቲዎች በተሰጠዉ መመሪያ መሠረት አንደ መመረያ ተዘገጅቶ በሴኔት ከፀደቀ ቦኃላ ቦርዱ እንዲያፃድቅ ተደርጎ ፀድቀዋል፡፡ ለተፈፃሚነቱ እንዲያመች በየደረጃ የሚገኙ የዩኒቨርሲቲዉ አመራሮች፤ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶችና እናቶች እንዲሁም የተማሪዎች ተወካይ ላይ የግንዘቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሰርቶ የካተቲ 17/ 2006 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ሙሉበሙሉ ታግባራዊ እንዲሆን ተደርገዋል፡፡

1.5. የሴት ተማሪዎቻችን ፆታዊ ትንኮሳ ለመከላካል በሁሉም ካምፓሶች በፀጥታና ፆታዊ ትንኮሳ ላይ ከፍተኛ ሥራ እየተሰራ ይጋኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅና በዋናዉ ግብ ሴት ተማሪዎቻችን ከከተማዉ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት ወደ ከተማ ስወጡ የሚደርስባቸዉን ፆታዊ ትንኮሳና ሌሎች የደህንነት ችግሮች እንዳይደርስባቸዉ ለመከላካል ስባል በካምፓሱ ዉስጥ እንዲያገኙ ለማድረግ የሴቶች የዉበት ሰሎን ተከፍቶ በተመጣጠኝ ዋጋ አገልግሎት እያገኙ ናቸዉ፡፡

1.6. በግቢ ዉስጥም ቢሆን ፆታዊ ጥቃት በተለይ ለሊት ላይ ሊኖር ይችላል ተብሎ ግምት ዉስጥ በማስገባት በሴት ተማሪዎች መኝታ አከባቢ የቤተመፅሓፍትና የኢነተረኔት አገልግሎት ኢንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡

1.7. የዩኒቨርሲቲዉ መምህራን-ተማሪዎች ግንኙነት፤ የሠራተኞች-ተማሪዎች ግንኘነትና የአመራሮች-ተማሪዎች ግንኙነት ጉዳይ ሰለማዊና ጤናማ እንዲሆን በየግዜዉ የግንዘቤ ማስጨበጫ ሥራ እየተሰራ ይጋኛል፡፡

1.8. ፆታዊ ትንኮሳዉን ለመከላከል የዩኒቨርሲቲዉ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ በተማሪዎቹ መካከል ከተማሪዎቹ በተወጣጡ የፆታዊ ትንኮሰ ተከላካይ ኮሚቴ ከሁለቱም ፆታ ተቋቅሞ በሰፊዉ እየተሰረበት ይጋኛል፡፡

1.9. በአገልግሎት መስጫ አከባቢም ምንም አይነት አድሎና ተመሳሰይ ችግሮች እንዳይኖር ለማድረግ ኡጋልግሎት ሰጪ ሠራተኞቻችን በ1 ለ5 በቡድን ተደራጅቶ አንዱ አንዱ ላይ ሂስ በማንሳት የተመጣጠነ አገልግሎት እየተሰጠ ይጋኛል፡፡ በተለይ በዩኒቨርሲቲዉ አብያተመጽሐፍት ኮሚቴ ተዋቅሮ ከግዜ ወደ ግዜ በአገልግሎት ላይ ያሉ ችግሮችን ነቅሶ በማዉጣት መፍተዎቻቸዉን እያስቀመጡ እየሰሩ ይጋኛሉ፡፡

1.10. በብሔር፡፤ በጎሳ፤ በሃይማኖት ልዩነት በዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ ዉስጥ እንዳይፈጠር በሀገረ ደረጀ በተከበረዉ ብሔር ብሔረሰብ ቀን በዩኒቨርሲቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥም ሁሉም የዩኒቨርሲቲዉ ማህብረሰብ በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ የተከበረ ሲሆን በክብረ በዓሉ ላይም ስለብዙሃንነትና አንድነት የግንዘቤ ማስጨበጫ ትምህርት በዩኒቨርሲቲዉ የበላይ አመራርና በሚመለከታቸዉ አካላት ተሰጥቷል፡፡

3.2.1.3. ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም

ዝርዝር ታግባራት፡-

- የተዘገጃዉ ሚዛናዊ ዉጤት ተኮር ዕቅድ ቤዘርፉ ላሉ የዩንቫርሲቲ አካላት እንዲወርድ ተዳገዋል፡፡
- በዚሁ መሠረት ሁሉም የአካዳሚክም ሆነ የአስተዳደር ሠራተኞች የየግል ዕቅደቸዉን አዘጋጅተዉ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡
- አፈፃፀሙ አዉቶሜሽን የተደገፈ ለማድረግ **የዩኒቨርስቲአችን የአይሲቲ ባለሙያዎች** BSC **ሶፍትዌሩን በተሳካ ሁኔታ□ ሠርተዉ □ ርስ□ል**፡፡
- በሶፍትዌሩ አጠቃቀም ላይ ለዩንቫርሲቲዉ መህብረሰብ ስልጣና ለመስጠት በወጠዉ ፕሮግረም **መሠረት በቅድሚያ ለሴኔት አባላት አግባብ ያለዉ ስልጠና ተሰጥቷል**
- በመቀጠልም የሁሉም ዘርፍ ኃላፊዎች የዩኒቨርስቲው ፕሬዚደንት ጭምር በተገኙበት ለሁሉም የት/ት ክፍል ኃላፊዎች ሁለት ዙር ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

- በቀ□□ በየኮሌጁች ያሉ የኢይሲቲ አስተባባሪዎች በየኮሌጃቸው ላሉ ለሁሉም ሠራተኞች ስልጠናውን በባለቤትነት እንዲሰጡ ለማድረግ እንዲችሉ ዝርዝር ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን በቅርቡ ሥራቸውን ያጠቃልላሉ፡፡

3.2.1.4. የካይዘን መሠረተ ሀሳብ አፈፃፀም ሪፖርት

□ር□ር ታግባራት

- የካይዘን መሠረተ ሀሳብና አተገባበሩን አስመልክቶ ከሁሉም ኮሌጆች፣ ከተማሪዎች አልግሎትና ክንብረት ክፍል ለተውጣጡ ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡
- በዚሁ መሠረት በሁሉም ንብረት ክፍሎች፣ መጋዘኖችና ወርክሾፖች የሚገኝ ንብረት ሁሉ በዓይነት በዓይነታቸው ተለይተው በአግባቡ ተደራጅተዋል፡፡ዝርዝር መለያም ተዘጋጅቶላቸዋል (labelled) ተ□ር□□ል፡፡
- በዚሁ መሠረት አብዛኞቹ ላቦራቶሪዎችና ንብረት ክፍሎች □እንዲሁም የሥራ ቦታዎች በተሻለ ሁኔታ□ ተ□ራፀ ተ□ል፡፡

ለማሳያ ያክል

1. **ግብርናና □እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ**

• □ተ□□ ክቃዎች ወ□□ዉኑ ለየጠያቂዎቹ □ተሠራፋ በመሆኑ በግብርናና □እንሳት ሕክምና ኮሌጅ ስቶር ዉስጣ በትርፍነት የሚቀመጥ ንብረት □ስም፡፡

በሌሎች ኮሌጆችና የሥራ ክፍሎች በተለይ ሆስፒታል የተፈጥሮ ሰይንስ ኮሌጂና ሌሎችም የተሻለ አፈፃፀም አሳይተዋል፡፡

□ተ□ኘ ውጤት

- **የንብረት አያያዝ ሥርዓቱ ከምንጊዜውም የተሻለ ነው፡፡**

- የአመለካከት ለውጥ ጎልብቷል፡፡
- መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት አሮጌ ንብረት ለማስወገድ ጥረት ተደርጓል

ያጋጠመ ችግር፡

መወገድ የሚገባቸው ብረታ ብረቶችና አሮጌ ጎማዎች ተለይተው ከተቀመጡ ብዙ ወራት የተቆጠረ ቢሆንም የሚያነሳው አካል ተገኝቶ ንብረቶቹን አለመረከቡ ዋናው ችግራችን ነው፡፡

ክፍል ሦስት

3.3.የግማሽ አመት የበጀት አጠቃቀም አፈፃፀም

በስድስት ወር ዉስጥ የበጀት አጠቃቀም አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲታይ 69.4 በመቶ የካፒታል በጀት እና 67 በመቶ ደግሞ በመደበኛዉ በጀት መጠቀም ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ከግመሽ በላይ የተፈፀመ ቢሆንም በተፈለገዉ ደረጃ ሊከናወን አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያዉ ሩብ አመት ክንዉን ከግማሽ በታች ስለተሰራ ነዉ፡፡ ሆኖም ግን የሁለተኛዉ ሩብ አመት ለብቻዉ ተናጥሎ ሲታይ የተፈለገዉ ያህል መጠቀም ተችሏል፡፡

ይህ አፈፃፀም በፕሮግራም ተነፃፅሮ ሲታይ፡-

የስራ አመራር በካፒታል 45.9 በመቶ በመደበኛዉ በጀት 69.4 በመቶ ደግሞ ተፈፅሟል፡፡

የመማር መስተማር 78.6 በመቶ

የጥናትና ምርምር 61.8 በመቶ

የማህበረሰብ አገልግሎት 65.1 በመቶ ሲሆን በጠቅላላ የግማሽ አመቱ አፈፃፀም 69.00 በመቶ ነዉ፡፡

ለአፈፃፀም ማነስ መሠረታዊ ምክንያቶች እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡-

የነበር ግንባታዎች መጓተት

የግዥ ወቅቱን ጠብቆ አለመገዘት

የመምህራን የምርምር ፕሮጀክቶች በወቅቱ ተገምግሞ አለመጠናቀቅ

የ2006 ዓ.ም. የግማሽ አመት የበጀት አጠቃቀም መግለጫ (በሺህ ብር)

የፕሮግራም ስም	ለበጀት አመቱ የታቀደ		ለ2ኛ ሩብ አመት የታቀደ ወጪ	የ2ኛ ሩብ አመት ዕቅድ አፈፃፀም	የግማሽ አመት ዕቅድ	የግማሽ አመት አፈፃፀም	የግማሽ አመት አፈፃፀም በመቶኛ
□ስራ አመራርና መልካም አስተዳደር	የከፒታል በጀት	912,427.20	347,384.70	371,287.95	680,217.20	471,985.10	**69.4**
	የመደበኛ በጀት	185,135.90	47,705.30	27,905.89	85,873.00	39,401.23	**45.9**
	ድምር	1,097.56	395,090.00	399,193.84	766,090.20	511,386.33	**66.75**
የመማርና መስተማር		-	-	-	-	-	
	የመደበኛ በጀት	352,094.00	86,944.89	57,918.27	160,034.99	125,708.41	**78.55**
	ድምር	352,094.00	86,944.89	57,918.27	160,034.99	125,708.41	**78.55**
የጥናትና ምርምር	የከፒታል በጀት	-	-	-	-	-	-
	የመደበኛ በጀት	12,754.00	2,876.26	1,879.39	5,261.55	3,064.39	**58.2**
	ድምር	12,754.00	2,876.26	1,879.39	5,261.55	3,064.39	**58.2**
የመማህብረሰብ አገልግሎት	የከፒታል በጀት	-	-	-	-	-	-
	የመደበኛ	108,330.50	23,577.77	14,826.52	45,115.82	29,358.55	**65.1**
	ድምር	108,330.50	23,577.77	14,826.52	45,115.82	29,358.55	**65.1**
አጠቃላይ ድምር	**የከፒታል በጀት**	**912,427.20**	**347,384.70**	**371,287.95**	**680,217.20**	**471,985.10**	**69.4**
	መደበኛ	**658,314.40**	**161,104.22**	**87,703.55**	**296,285.36**	**197,532.58**	**66.7**
	ድምር	**1,570,741.60**	**508,488.92**	**458,991.50**	**976,502.56**	**669,517.68**	**68.56**

ክፍል አራት

3.2.አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች መረጃ

ፕሮግራም	ቅድመ ምረቃ	ድህረምረቃ ዲፕሎማ	ድህረ ምረቃ	ድምር
መደበኛ	19414	286	2378	22078
ክረምት	6386	949	811	8146
ማታ	2987	-	229	3216
ርቀት	12050	-	-	12050
ድምር	40837	1235	3418	45490

አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲዉ የተማሪዎች መረጃ በግራፍ (በ2006 የትምህርት ዘመን)



ምስል ቁጥር-6



ከምስሉ እንደሚታየዉ መንግስት የትምህረት ፖሊስ ስቀርፅ ሀገራችን ለወደፊቱ ኢንደስተሪን ያማከለ ኢኮኖሚ ስለምኖራት ከወዲሁ የዩኒቨርሲቲ ቅበላ ስረዓት የቴክኖሎጂና ተፈጥሮ ሰይንስ ለማህብራዊ ሰይንስ ያላቸዉ ቀመረ 70፤30 መሆን እንደለበት መንግስት በፖሊስ ዉስጥ ከማስቀመጥ በሻገር ተፈፃሚም እንዲሆን አድርጎ በዚሁ መሠረት ዩኒቨርሲቲያችንም ስተገበር ቆይተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ከግራፉ ኢንደሚተያዉ 82 በመቶዉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎች ሲሆኑ ቀሪዉ 18 በመቶዉ ደግሞ የማህብራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ይህ ቁጥር መንግስት ከስቀመጠዉ ቀመረ ጋር ስነፃፀር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎች በ12 በመቶ አልፎ ሲገኝ የማህበራዊ ሳይንስ ደግሞ በ12 በመቶ ዝቅ በሏል፡፡ ሆኖም ግን ሙብለጡ በበጎ ጎኑ ቢታይም ለወደፊቱ የማህብራዉ ሣይንስ ተመራቂዎች እየመንመነ ስላሚመጣ ዩኒቨርሲቲዉ ይህንን ግንዘቤ ዉስጥ በማስገባት ወደ ማህብራዊ ሳይንስ አከባቢ ተፈላጊ የሆኑ የትምህርት መስኮችን በመለየት ካርኩለም እየቀረፀ በማከፈት ተማሪዎችን እየተቀበለ ነዉ፡፡

የሴት ተማሪዎች ቅባላ ከመጨመር አንፃር አሁን ያለዉ የሴት ተማሪዎች ድርሻ ሲታይ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

ምስል ቁጥር-7



የክንዉኑ ዝርዝር መግለጫ፡-

በምስል ቁጥር-7 እንደሚንመለከተዉ ዩኒቨርሲቲያችን በሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ምን እንደምመስል ለመወቅ በተደረገዉ ጥናት ከዋናዉ ሬጂስትራር በተገኘዉ የዚህ ዓመት መረጃ በመደበኛዉ መረሀ-ግብረ ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ የሚገኙ ሴት ተማሪዎች 22 በመቶ ሲሆኑ ቀሪዉ 78 በመቶዉ ወንድ ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ይህ ቁጥር ከ2005 የትምህርት ዘመን 22-18= በ4 በመቶ ጨምሯል፡፡ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲዉ ካለዉ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ማሳደግ ጋር ተያይዞ ይህ ቁጥር ትንሽ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲያችን የሴት ተማሪዎች የመመረቂያ ምጣኔ በእጅጉ ለመጨማርና በዩኒቨርሲቲ ዉስጥ ቆይታቸዉንም ለማሰደግ የሚያደርገቸዉ ጥረቶች ይህ ነዉ የማይባል ነዉ፡፡ ከዚህ ዉስጥ በጥቂቱ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸዉ ሴት ተማሪዎች በመለየት ፡- የኢኮኖሚ ድገፌ ማድረግ፤ አገልግሎቶችን ወደ መኝታ ቤታቸዉ አከባቢ እንዲቀርብ በማድረግ፤ የፆታ ትንኮሳ እንዳይደርስበቸዉ የፀና ክትትል በማድረግ፤ የማጠናከሪያ ትምህርት በማስጠትና ሌሎችም ናቸዉ፡፡ የተማሪዎቹ ቁጥር በተፈለገዉ ደረጃ መጨማር ያልቻለበቸዉ ምክንያቶች አንደኛ ዩኒቨርሲቲዉ የተሸለ አፈፃፀም ስለምያሳይ፤ ለተማሪዎቹ ጥሩ አገልግሎት ስለምሰጥ፤ ጥራቱንና አግባብነቱን የጠበቀ የትምህረት አሰጣጥ ስረዓት ስለዘረጋና በሌሎች ምክንያቶች የሀገር አቀፍ ፈተና ያለፉ ተማሪዎች በአብዘኛዉ ይህን ዩኒቨርሲቲ በመጀመረያ ደረጃ ስለምመርጡና ከፍተኛ ዉጤት ያለቸዉ ተማሪዎች በቅዲሚያ የማግኘት ዕድላቸዉ ካፍ ይላል፡፡ በሀገራችን አሁን ባለዉ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ በአብዘኛዉ ወንድ ተማሪዎች ከፍተኛ ዉጤት እንደሚያስመዘግቡ ግልፅ ነዉ፡፡ ስለሆነም የጂማ ዩኒቨርሲቲ የማግኘት ዕድላቸዉ ካፍ ይላል፡፡ በዚህና በሌሎች ምክንያቶች የሴት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የመምጣት ዕድላቸዉ በጣም ያነሰ ስለምሆን ቀድሞዉኑ ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የሚገቡ የሴት ተማሪዎች ቁጥር በጣም ትንሽ ነዉ ማለት ነዉ፡፡

ክፍል አምስት

3.3. የነባር ካፒታል ፕሮጀክቶች ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ምስል ቁጥር -8፡ የዋና ግብ የካፒታል ፒሮጀክቶች ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም



	የትኮንግሪፍሪል ሆሲፒታል ግንባታ	የተጨማሪ ፋሲልት ግንባታ	የመማሪያና ሲቭክ አደራሽ ግንባታ	የመከና መቆሚያ ጋናባታ	የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ግንባታ	የዉሃ ኔትዎረክ ግ ግንባታ	የማስፋትና አድስ የጉድገድ ዉሃ ቁፋሮ	የሊፍት ገጠማ
አሁን ያለቡት ደረጃ	88.60%	70.09%	87.45%	91.94%	90.34%	33.31%	0%	0%
የግማሽ አሙት ዕቅድ	21.14%	31.76%	24.13%	28.92%	9.66%	81.76%	0%	0%
የግማሽአሙት አፈፃፀም	8.26%	7.85%	11.60%	14.40%	6.28%	1.92%	0%	0%

በቴክኖሎጂ ካምፓስ (ክቶ ፉርዲሳ ካምፓስ) እና በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ የሚገኙ የካፒታል ፕሮጀክቶች ግንባታ አፈፃፀም በመቶኛ ስሌት

ምስል ቁጥር-9 የክቶ ፉርዲሳና ግብርናና እንስሰት ህክምና ኮሌጅየፕሮጀክቶች ግንባታ



	የመማሪያ ክፍልና ክልንክ ግንባታ	የቢሮዎች ግንባታ	ዎርክሾፕና ላቦራቶሪ ግንባታ	ሳይት ዎርክ(መንገድ፤ ማበራት)	የተማሪዎች መማሪያ ክፍል ሎት-2 ግንባታ	ዶሪምቶሪ ሎት-2	ሳይት ዎርክ(ዉሃ፤አጥር)	ግብርና ኮጅ ቢሮና ቤተመፅሐፍት ግንባታ
አሁን ያለበት ደረጃ በመቶኛ	96.70%	65.13%	53.56%	69.21%	94.48%	78%	97.08%	80.67%
የማሻሸ አሙት ዕቅድ በመቶኛ	6.30%	45.69%	30.84%	39.16%	30.31%	56.91%	8.29%	34.52%
የማሻሸአሙት አፈፃፀም በመቶኛ	9.07%	10.30%	30.80%	33.90%	50.80%	11.14%	8.95%	10.60%

ክፍል ስድስት

3.4. ለዕቅድ አፈፃፀሙ መሳካት የተደረጉ የክትትልና ግምገማ ስርዓቶች

በየደረጃው ያሉ የዩኒቨርሲቲው አካላት ለዕቅዱ ተፈፃሚነት የተለያዩ ጥረቶችን አድርገዋል፡፡

- የስራ ክፍሎች የየራሳቸውን ዕቅድና አፈፃፀም የሚገመግሙ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ካውንስልም ዩኒቨርሲቲ አቀፍ ግምገማ አድርጓል፡፡
- የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራርም ደረጃ በደረጃም ቦርዱ፡ የተወካዮች ምክር ቤት፡ የትምህርት ሚ/ርና መሰል ተቋማት በሚቀርብላቸው ዕቅድና ሪፖርቶች ላይ በመመስረት የሚሰጡት ግብረ መልስና ጠቃሚ አስተያየቶች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ □እንዲደርሰው ተደር□ል፡፡

ምዕራፍ አራት

4. የግማሽ ዓመት አፈፃፀም ማጠቃለያና የዩኒቨርሲቲው ቦርድና ካዉንስል ግምገማ

የ2006 ዓም የዩኒቨርሲቲው ዕቅድ ባለፉት ዓመታት የተገኙ ልምዶችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን ለአተገባበርና ክትትል አመችነት ሲባል በዝግጅት፡ ትግበራ እና ማጠቃለያ ምዕራፎች የተከፋፈለ መሆኑ ይታወሳል፡፡

የዝግጅት ምዕራፍ ከሐምሌ እስከ መስከረም መጨረሻ ባሉት የበጀት አመቱ የመጀመሪያ ሶስት ወራት የሚከናወን ሲሆን ይህ ምዕራፍ የትምህርት አመቱ አግባብ ባለዉ መልክ ይከናወን ዘንድ የሚያስችሉ የተለያዩ አስተዳደር ነክና ከመማር ማስተማር ጋር የተያያዙ የዝግጅት ስራዎች የተከናወኑበት ወቅት ነበር፡፡ በመሆኑም በዚህኛዉ ሩብ ዓመት ግን አብዘኛዉ የመማር መስተምርም ሆነ ሌሎች ቁልፍ ታግባራት የተከናወኑበት የትግበራ ምዕራፍ ነዉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ተገቢዉ የአፈፃፀም ስራዎች የተሰሩበት በመሆኑ ለቀጠዩ የትግባራ ምዕራፍም መሠረት የጠለ ምዕራፍ መሆኑን የዩንቨርሲቲዉ አመራር ያምናል፡፡ ይህም ማለት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የዩኒቨርሲቲው አመራር ቦርድን ጨምሮ ያለፈው ዓመት አፈፃፀምን በመገምገም ለበለጠ አፈፃፀም በጋራ መግባባት በመነሳት ለመስራት ቃል ተግባብተው የተንቀሳቀሱበትና ለውጤት የበቁበት ምዕራፍ ነዉ፡፡

ይህ ማለት ግን የታቀዱት ስራዎች ሙሉ በሙሉ ተተግብረዋል ወይም ምንም ችግር አልተፈጠረም ማለት አይደለም፡፡ በሁሉም ፕሮግራሞች ማለት ይቻላል ከዕቅዱ አንስተው የተፈፀሙ፡ ሙሉ ለሙሉ ያልተከናወኑ ተግባራት እንዳሉና ለእነዚህም ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች አስተዋፅዎ ማድረጋቸውን አመራሩ ይረዳል፡፡ ዋናዋዎቹም ሚከተሉት ነበሩ፡፡

- የቲቺንግ ሪፈራል ሆስፒታሉ ግንባታ የመጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ቢሆንም ስራ ሊያስጀምር የደረሰበት ደረጃ አይደለም፡፡
- በተማሪዎች የምግብ ግብዓቶች ዋጋ ንረት ምክንያት ለነብስወከፍ የተመደበዉ በጃት በቂ አለመሆን እስከሁን ድረስ የሚታዩ ችግሮች ናቸዉ
- የከፍተኛ ደረጃ መምህንንን ከሃገር ውስጥ ገበያ መሟላት አለመቻሉ በተለይ በቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩትና በቢዚናስና ኢኮኖምክስ ኮሌጅ
- የዉሃ ዕጥረት በሰፊዉ ስለመተየቱና በዕቅድ አፈፃፀማችን ላይ ተፅዕኖ በማሰደሩ
- በግዥ መዘግየት ምክንያት አንዳንድ በወቅቱ ሊከረናወኑ የሚገባቸው ሥራናዎች መጓተታቸው
- የአቅራቢዎችና ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት ግደታቸውን አለመወጣት
- ሆኖም ግነ በቀጣዮቹ ሩብ አመታት በከፍተቶቻችን ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድና ከተለያዩ አካላት ጋር በተጠናከረ ሁኔታ አብሮ በመስራት ችግሮቹን ቀርፈን ወደላቀ አፈፃፀም እንደምንሸጋገር እምነት አለን፡፡